## ለ/ የጣልያን አስተያየት፣

ባለፈው ዓመት ስኞ ህዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም ከአኩለ ቀን በኋላ በአሥር ሰዓት፣ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ፍጻሜ ላይ፣ ለኤርትራ ሕዝብ መርማሪ ኮሚሽን እንዲመደብለት፣ ሱማሌን፣ ጣልያን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድራት በተወሰነ ጊዜ፣ የሮማ መንግሥት ዋና ወኪል አምባሳደር አልቤርቶ ታርኪያኒ፣ ለደጋስፐሪ ባስተላለፈው ቴሌግራም፣ « ..... ድሉ ለጣልያን ! ..... ሀዘኑ ለኢትዮጵያ ! ...... » ሆኗል ሲል፣ የገለጸውን አስተያየት ታሪክ ለመቸውም አይረሳውም። በመሠረቱ አልቤርቶ የተናገረው ከእውነት የራቀ አይደለም። ከዚያ ሁሉ ድካምና ከዚያ ሁሉ ጥረት በኋላ፣ የተባበሩት መንግሥታት፣ ጣልያን በነደፈው ሀሳብ ተመርቶ የሰጠው ውሳኔ፣ ለኢትዮጵያ እጅግ የመረረ ቅሬታ፣ ለሮማ መንግሥት ገደብ የሌለው ደስታ እንደሰጠ አይካድም።

ጣልያን፣ ምንም እንኳ የተባበሩት መንግሥታት የአባልነት መብት ባይኖራት፣ በጀርባ ሆና የምትተበትበው ተንኮል ሁሉ የምትፈልገውን ውጤት ስለሰጣት፣ በዚህ በህዳር 21 ቀን የአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ባደረገው ውሳኔ፣ ምን ያህል እንደተደሰተችና ወደፊትም በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ዕምነት እንደምታሳድር በመግለጽ፣ የመንግሥቱ መሪ አልቺደ ደጋስፐሪ ለኒውዮርክ ያስተላለፈው ቴሌግራም እጅግ የጋለ እንደነበረ እናስታውሳለን።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም በበኩላቸው ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በላኩት ቴሌግራም፣ « ...... በመንግሥታት ማህበር አባሎች መካከል የሚፈጸመው ጥቃቅን ጥቅም፣ ትክክለኛ ፍርድን እንዴት አድርጐ እንደሚያዛባ፣ አንድ ቀን « እውነት » የተሸፈነውን ገልጦ ድል የሚመታበትን ጊዜ ለማየት እንደምበቃ፣ ያለኝን ጽኑ ዕምነቴ የመልዕክቴ መደምደሚያ አደርገዋለሁ ...... » ብለው ነበር። በመሠረቱ፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኩል፣ ተፈርዶለት ለሚዝናናውም ሆነ ተፈርዶበት ለሚበሳጨው፣ የስሜት ተካፋይነት መግለጫ ወግና ልምድ ስለሌለ፣ ለሚደርሱት ለማናቸውም መልዕክቶች የድርጅቱ ዋና ፀሐፊ መልስ አይሰጥም። የዚህ ዓለም ሂደት እንደሚያሳየው ዛሬ የተደሰቱት ነገ ምን ሀዘን ላይ እንደሚወድቁ፣ ዛሬ ያዘኑት ደግሞ ነገ ምን ደስታ እንደሚያገኙ መተንበይ ስለማይቻል፣ ጊዜው የሚፈጥረውን ለማየት፣ ትዕግሥትና እርጋታ ከሁሉም የበለጠ መድኃኒት ይሆናል።

የሮማ መንግሥት፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጀርባ ሆኖ በሚሠራው ተንኮል፣ ለኤርትራ መርማሪ ኮሚሽን አባል ሆነው ከተመረጡት አምስቱ ዳኞች መካከል፣ ጓቴማላ፣ ፓኪስታንና ደቡብ አፍሪካ ደጋፊዎቹ እንደሚሆኑ እርግጠኛነት ተሰምቶት፣ አራተኛውን የበርማን ወኪል በጉቦ ለመግዛት በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ትክክለኛ ፍርድ ይሰጠኛል ብላ የተማመነችው በአንድ በኖርዌዩ ዳኛ ብቻ ነበር። ኢትዮጵያ ! ታበፅሀ እደዊሐ ኀበ እግዚአብሔር እንደተባለው፣ ለዚች አገር አምላክ የሚሠራላት ተአምሩ ብዙ ስለሆነ፣ የጣልያን ወገን ነው ተብሎ እምነት የተጣለበት ደቡብ አፍሪካና፣ በገንዘብ ጉቦ ፍርዱን እንዲሸጥ ዶላር የተዘጋጀለት የበርማ ኮሚሽነር፣ ከኖርዌይ ጋር ሆነው አስተያየታቸውን በማስተባበር የሮማን መንግሥት ዕቅድ አፈረሱበት።

ጓቴማላና ፓኪስታን፣ ጣልያን የሰጣቸውን መምሪያ ተከትለው፣ ኤርትራ ከነፃነት በፊት ለአሥር ዓመታት የሮማ መንግሥት በሞግዚትነት እንዲያስተዳድራት ቢታገሉም፤ አብዛኛዎቹ ዳኞች፣ የኤርትራ ሕይወት ከኢትዮጵያ ተለይቶ መኖር እንደማይችል የሰጡት አስተያየት፣ በዓለም ጉባኤ ፊት ትክክለኛ ሆኖ ተደመጠ:: የተባበሩት መንግሥታት ጊዜያዊ ኮሚቴ (INTERIM COMMITTE) ከበርማና ከደቡብ አፍሪካ የቀረበውን የፌዴሬሽን መፍትሔ ተስማምቶ ለዋናው የፖለቲካ ኮሚሲዮን ሲያቀርብ፤ እዚያም ላይ የሮማ መንግሥት ሀሳቡን የሚከተሉለት ሊያገኝ አልቻለም::

የፖለቲካው ኮሚሲዮን ጉዳዩን በሚመረምርበት ጊዜ፤ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር ጁሴፔ ብሩዛስካ፣ (GIUSEPPE BRUSASCA) በቀቢጸ ተስፋ፣ ያደረገው ንግግር፣ የጣልያንን መንቀዥቀዥና ጤና ማጣት የሚያመለክት ነበር:: ጓቴማላና ፓኪስታን፣ ለኤርትራ ነፃነት የሚገባት መሆኑን ያረጋገጡት፤ በርማ እና ደቡብ አፍሪካ የፌዴሬሽን መፍትሔ ይሻላል ያሉት፤ ኤርትራ፣ በኢትዮጵያ አስተዳደር ውስጥ እንዳትዋጥ አስበው መሆኑን ኮሚሲዮኑ እንዲገነዘበው፤ ጁሴፔ ብሩዛስካ በዲስኩሩ እየተዝናና ሲናገር፣ የሚታዘበኝ ይኖር ይሆን ? ብሎ አልተጨነቀም ነበር:: የጣልያን መልዕክተኛ በዚሁ መግለጫው ውስጥ፤ ከአምስቱ መርማሪ ኮሚሽን አባሎች መካከል አራቱ፣ የኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር መዋሀድ ተቃውመዋል ብሎ ያለ አፍረት ሲናገር፤ ለወጉ እንኳን፣ አምስተኛው ዳኛ የኖርዌዩ ኮሚሽነር፣ ምን አስተያየት እንዳቀረበ ሊጠቅሰው አልፈለገም::

ጓቴማላና ፓኪስታን የሰጡት ፍርድ፣ ለኤርትራ የወደፊት ዕድል ምን ያህል ጠቃሚና ትክክለኛ መሆኑን ካሟሟቀ በኋላ፤ በርማ፣ ደቡብ አፍሪካና ኖርዌይ ያቀረቡትን ሀሣብ፤ ጁሴፔ ብሩዛስካ በራሱ አመለካከት ተርጉሞ የኮሚሲዮኑን አባሎች ለማወናበድ የመጨረሻ ጥረት ያደረገው፤ የፌዴሬሽኑ መፍትሔ ተቀባይነትን እንዲያጣ ለማድረግ ነበር:: መጀመሪያ፣ ጉዳዩ በጊዜያዊ ኮሚቴ ተጠንቶ የተደረገው ስምምነት፣ አሁን ደግሞ በዋናው የፖለቲካ ኮሚሲዮን ላይ የሚዘጋጀው ውሳኔ፣ ከሮማ መንግሥት ምኞትና ፍላጐት አጅግ እየራቀ መሄዱን ሲያውቀው፤ ስለ ፌዴሬሽኑ መፍትሔ የጣልያን አስተያየት ሊደመጥ ይገባል በማለት፣ ብሩዛስካ በመጨረሻ ያቀረበው ሀሣብ የሚከተለው ነበር::

« ...... የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኤርትራን ጉዳይ ለመወሰን፣ ከኢትዮጵያ ጋር የፌዴሬሽን አስተዳደር መመሥረቱ ይሻላል ብሎ ካመነበት፣ በኤርትራ የሚኖሩት ጣልያኖች ውሳኔውን የሚያከብሩና በትክክል የሚፈጽሙ መሆናቸውን እናረጋግጣለን:: ...... ነገር ግን የፌዴሬሽን አስተዳደር የሚደገፈው፣ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር እውነተኛ የኤርትራ መንግሥት እንደሚቋቋምና፣ ሕዝቡም በፖለቲካና በኢኮኖሚ ልማት በትክክል የሚኻፈልበት እንደሚሆን ተስፋ በማድረግ ነው:: ..... በፌዴሬሽኑ ሕግ፣ ለኤርትራ መንግሥት የሚሰጠው ሥልጣን፣ በውስጥ አስተዳደር ላይ የተወሰነ ብቻ ሳይሆን፣ በውጭ ፖለቲካና በውጭ ንግድ ግንኙነት ጉዳይ፣ ተገቢውን መብት የሚያገኝና፣ በመከላከያም ረገድ የውጭ ጠላት ቢመጣበት ለመመከት የሚያስችል ኃይል ሊኖረው ይገባል ...... »

ከዚህ በላይ እንደታየው የጣልያን የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር፣ ስለ ፌዴሬሽኑ አሠራር የሰጠው አስተያየት፤ በበርማና በደቡብ አፍሪካ የቀረቡትን

መሠረታዊ ነጥቦች የሚደመስስና፣ አንድ አዲስ አገር ነፃ መንግሥት ሆኖ ሲቋቋም የሚኖረውን፣ ያገር ውስጥና የውጭ ፖሊሲን ሥልጣን የሚተነትን ስለሆነ፣ ከሚሲዮኑ ከሚያዘጋጀው ከፌዴሬሽን መፍትሔ ጋር የሚቀራረብ አልሆነም።

ሴናተር ብሩዛስካ፣ በአንድ በኩል ለኤርትራ ጉዳይ፣ ከነፃነት በስተቀር ሌላ መፍትሔ የለም እያለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፌዴሬሽኑን መቀበል እንደሚቻል ሲያረጋግጥ፤ በሁለቱ መፍትሔዎች መካከል ያቀረባቸው የተወሳሰቡ ሀሳቦች ከብስጭትና ከተስፋ መቁረጥ የተነሣ ስለሆነ፤ ከሚሲዮኑ በቁም ነገር ሊመለከተው አልቻለም።

በፖለቲካው ከሚሲዮን ላይ ጓቴማላና ፓኪስታን፣ ለኤርትራ ነፃነት እያሉ ሲጮኹ፤ ቀድሞ ለጣልያን ሲሟገቱ ከነበሩት፤ የላቲን አሜሪካ አገሮች መካከል አሥራ ሁለቱ፤ ጥንታዊ አቋማቸውን ለውጠው የፌዴሬሽን መፍትሔ ደጋፊዎች ሆኑ። ይህም ሊሆን የቻለው የብራዚልና የሜክሲኮ መልዕክተኞች አምባሳደር ሙንዚ እና አምባሳደር ኔርቮ (MUNZI AND NERVO) የጊዜያዊው ከሚቴ ሊቀመንበርና ምክትል ሆነው የኤርትራን ጉዳይ ባጠኑበት ጊዜ፤ የኢትዮጵያን አቋም ትክክለኛነት ስለተገነዘቡ፤ የአብዛኛዎቹንም ዳኞች አስተያየት መከተል ተገቢ መሆኑን ስለአመኑበት፤ እነዚህ ሁለት ሰዎች በወገኖቻቸው በላቲኖቹ ዘንድ ባደረጉት የማግባቢያ ጥረት መሆኑ ይነገራል።

ለኤርትራ ጉዳይ መፍትሔ ናቸው እየተባሉ ከልዩ ልዩ አባል አገሮች ለፖለቲካው ከሚሲዮን የቀረቡት ረቂቅ ውሳኔዎች፤

1. የተለመደው የሶቪየት ሕብረትና የፖላንድ የተቃውሞ ሬዞሉሽን፣

2. የፓኪስታንና የጓቴማላ የነፃነት ጥያቄ፣

3. የኤርትራ ሕዝብ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ከመሆንና ነፃነትን ከመቀበል የትኛው እንደሚሻለው <u>በድጋሚ እንዲጠየቅ ከኢራቅ የቀረበው ሀሳብ፣</u>

4. ኤርትራ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘውድ ሥር፣ የውስጥ አስተዳደር መንግሥት አቋቁማ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትዋሀድ፤ ዩናይትድ ስቴትስና ሰባት የላቲን አሜሪካ አገሮች ተካፋይ የሆኑበት፤ <u>የአሥራ አራት አባል መንግሥታቶች የጋራ ረቂቅ ውሳኔ፤</u> ናቸው።

ይህ በአራተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው፤ በቦሊቪያ፣ በብራዚል፣ በበርማ፣ በካናዳ፣ በዳንማርክ፣ በኤኳዶር፣ በግሪክ፣ በላይቤሪያ፣ በሜክሲኮ፣ በፓናማ፣ በፓራጓይ፣ በፔሩ፣ በቱርክ እና በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ፣ ተቀነባብሮ የቀረበው የጋራ ረቂቅ ውሳኔ፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የምትዋሀድበትን ዝርዝር ሁኔታ አብራርቶ የሚገልጽ ነበር። ይኸውም፤ የፌዴራሉ መንግሥት የሆነችው ኢትዮጵያ፤ በመከላከያና በውጭ ጉዳይ፣ በፊናንስና በንግድ፣ በመገናኛዎችና በወደብ አስተዳደር ሙሉ ሥልጣን ሲኖራት፤ የኤርትራ የውስጥ መንግሥት ደግሞ፣ ከነዚህ ለፌዴራሉ መንግሥት ከተዘረዘሩት ድርሻዎች ውጭ በሆኑት ጉዳዮች ላይ በሙሉ ኃላፊነት ያስተዳድራል የሚል ነው።

በእነዚህ በአሥራ አራት አባል አገሮች ተዘጋጅቶ፣ ለፖለቲካው ኮሚሲዮን የቀረበው የጋራ መፍትሔ፤ ከሌሎቹ ጋር ተወዳድሮ በሠላሳ ስምንት (38) የአባል አገሮች ድምፅ ብልጫ አሸናፊ በመሆኑ፤ የመጨረሻውን ውሳኔ እንዲያገኝ ህዳር 30 ቀን 1950 ዓ.ም ለጠቅላላው ~~ጉባኤ ተላለፈ~~:: የጣልያን መንግሥት በቅኝ ግዛትም መልክ ሆነ በሞግዚት አስተዳደር፤ ኤርትራን መልሶ ለመያዝ ለአምስት ዓመታት ያለማቋረጥ ሲደክምበትና ሲታገልበት የኖረው ትልቁ ምኞቱ ሞቶ፤ ግብዓተ መሬቱ የተፈጸመው በዚህ ህዳር 30 ቀን 1950 ዓ.ም የፖለቲካው ኮሚሲዮን ባደረገው ውሳኔ ነው ማለት ይቻላል::

## የመጨረሻው ውሳኔ

በኢትዮጵያ አቆጣጠር ቅዳሜ ህዳር 23 ቀን 1943 ዓ.ም፣ (በአውሮፓ ዘመን አቆ/ታህሣሥ 2 ቀን 1950) የአምስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የኤርትራን የወደፊት ዕድል በድምፅ ብልጫ የሚወስንበት ታሪካዊ ዕለት ነበር::

የጉባኤው ሊቀመንበር የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ናስሮላህ ኢንተዛም፤ (NASROLLAH ENTEZAM) ስብሰባውን ሲከፍት በለጠው አጭር መግለጫ፤ « .... ለኤርትራ ጉዳይ የመጨረሻውን መፍትሔ ለመስጠት፤ ከሶቪየት የፖለቲካው ኮሚሲዮን አጥንቶ ያቀረበልንን ረቂቅ ውሳኔ፤ እንዲሁም ከሶቪየት ሕብረት፤ ከፖላንድ እና ከኢራቅ በቀረቡት ሀሳቦች ላይ፣ ጉባኤው በየተራ ድምፅ እንዲሰጥበት እጠይቃለሁ ...... » አለ:: ወዲያው ከሊቀመንበር ናስሮላህ መግለጫ በኋላ፣ ጉባኤው ሥራውን ከመቀጠሉ በፊት፤ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የመጀመሪያው ተናጋሪ ሆነው፣ ለውሳኔ በቀረበው ጉዳይ ላይ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት አቋምና አስተያየት ለማስረዳት እንዲፈቀድላቸው ጠየቁ:: ቃሉም የሚከተለው ነበር::

« ...... ለብዙ ዓመታት ፋታ ያልሰጠ ምርምርና ጥናት ሲደረግበት የኖረው የኤርትራ ሕዝብ የወደፊት ዕድል፤ ብዙ ፈተናዎችና መሰናክሎችን ካሳለፈ በኋላ፣ ዛሬ በዚህ እጅግ በተከበረው የዓለም ሸንጎ ላይ፣ የተባበሩት መንግሥታት እንደራሴዎች የመጨረሻ ፍርዳቸውን እንዲሰጡበት ተጠይቀዋል:: ይህንን በዛሬው ዕለት የሚሰጠውን ፍርድ ለመስማት፤ እጅግ በጋለና በተጨነቀ መንፈስ የሚጠባበቀው፣ ባለጉዳዩ የሆነው ወንድማማቹ የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፤ ነፃነትና ትክክለኛ መብት ለማግኘት በትዕግሥትና በተስፋ የሚኖሩት ወገኖቻችን፣ አፍሪካውያኖች ጭምር መሆናቸውን የምናገረው፤ ከልብ በመነጨ እውነተኛ ስሜት ነው::

ሊቀመንበራችን የጉባኤውን ሥራ ከከፈቱ በኋላ፤ የተከበራችሁ የዓለም መንግሥታት እንደራሴዎች የመጨረሻ ፍርዳችሁን ከመስጠታችሁ በፊት፣ የመናገር ዕድል እንዲሰጠኝ ያመለከትኩት፣ ከፖለቲካው ኮሚሲዮን ተዘጋጅቶ በቀረበላችሁ ውሳኔ ላይ፣ የኢትዮጵያንና የሕዝቧን፣ የንጉሠ ነገሥቷንና የመንግሥቷን አስተያየት በቅድሚያ እንድታውቁት በማሰብ ስለሆነ፤ የተነሳሁበትን ዓላማ ቅን በሆነ መንፈስ እንደምትረዱልኝ ሙሉ ዕምነት አለኝ::

...... ለውሳኔ ተዘጋጅቶ ከፊታችሁ የቀረበው መፍትሔ፣ የአብዛኛውን የኤርትራ ሕዝብ ፍላጐትና የኢትዮጵያን ጥያቄ ፍጹም የሚያረካ አለመሆኑን፤ ከጥቂት ቀናቶች በፊት ለፖለቲካው ኮሚሲዮን መናገሬን፣ ዛሬ ለዚህ ለተከበረው ጠቅላላ ጉባኤ መደበቅ አልፈልግም:: ይሁን እንጂ፤ አሁን ባለንበት ጊዜ የኤርትራን ጉዳይ ለመወሰን፣ ከዚህ ከቀረበው የፌዴሬሽን መፍትሔ የተሻለ፣ ለማናቸውም ወገን አስታራቂና አግባቢ የሆነ፣ አማራጭ መንገድ አለመኖሩን በጥልቅ ስለተገነዘብኩ፤ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትና በሕዝቡ ስም ሆኜ፣ ያለ አንዳች ቅሬታ በሙሉ የምቀበለው መሆኔን ለተከበረው ጉባኤ በይፋ አረጋግጣለሁ:: ...... በፖለቲካው ኮሚሲዮን ከብዙ ውይይትና ከብዙ ጥናት በኋላ፣ በአሥራ አራት መንግሥታቶች የተቀነባበረው ሀሳብ፣ እጅግ ከፍተኛ በሆነ የድምፅ ብልጫ አሸናፊ ሆኖ የቀረበላችሁን፤ ይህን የፌዴሬሽን መፍትሔ ለማጽደቅ የቆረጣችሁ ከሆነ፣ ኢትዮጵያና የንጉሠ ነገሥቷ መንግሥት፣ የተባበሩት መንግሥታትን ውሳኔ እንከን በማይወጣለት ሥርዓት የሚያከብሩትና በትክክል በተግባር ላይ የሚያውሉት መሆኑን የምገልጽላችሁ፣ በማያጠራጥር እውነተኛ በሆነ ስሜት ነው::

...... ለዚህ ለተከበረው ጠቅላላ ጉባኤ፣ ኢትዮጵያና የንጉሠ ነገሥቷ መንግሥት በተጨማሪ ዋስትና ለመስጠት የሚፈልጉት፣ ከእንግዲህ ወዲህ በኤርትራ ውስጥ ያሉት እስላሞች እና ክርስቲያኖች፣ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ የውጭ አገር ዜጐችና ተወላጆች፣ የተባበሩት መንግሥታት በሚያምንበት የዲሞክራሲ ሥርዓት፣ በሕግ የተረጋገጠው መብታቸውና ነፃነታቸው በትክክል የሚከበርላቸው መሆኑን ነው::

...... በትግሉ ዘመን በልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ስለ ኤርትራ የወደፊት ዕድል የተለያዩ አቋሞች ይዘው፣ አንድነታችንን የደገፉትም ሆኑ የተቃወሙት፣ ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው፣ በኤርትራ ውስጥ ሆነ በኢትዮጵያ፣ በማናቸውም የመንግሥት የሥራ መስክ ላይ ሆነ የግል ድርጅት፣ መብታቸው የሚፈቅድላቸውን ለማግኘት አንዳችም እንቅፋት እንደማይገጥማቸው ለማረጋገጥ እወዳለሁ::

...... በኤርትራ ውስጥ ከእንግዲህ ወዲህ በሕዝቡ መካከል፣ አብዛኛዎችና አነስተኞች ተብሎ የሚከፈል ግሩፕ፤ የእስላምና የክርስቲያን እየተባለ የሚለይ የአውራጃና የወረዳ ግዛት፤ በትግሉ ዘመን የአንድነት ደጋፊ ሆኖ የዘለቀ፣ ወይም የተቃዋሚዎች መሣሪያ የነበረ በሚል ስያሜ የሚከፋፈል ወገን፣ ጨርሶ እንደማይኖር መታወቅ አለበት:: መላው የኤርትራ ሕዝብ፤ በዘርና በሀይማኖት ሳይለያይ፣ በወንድማማችነት መንፈስ ተሳስሮ፣ በእኩልነትና በጋራ ኃላፊነት፣ ለአገሩ ልማትና ለራሱ ዕድገት እንዲጥር፣ የተባበሩት መንግሥታት የቀየሱለትን መንገድ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት መልካም አስተያየቱንና እምነቱን እንደአሳረፈበት ለማስገንዘብ እፈልጋለሁ:: ...... ለዚህ ሁሉ መሠረቱ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ለኤርትራውያን ወንድሞቻቸው በመሆናችን፣ ኤርትራውያኖችም የኛ የኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን በመሆናቸው፤ የጋራ የሆነው ታሪካችንና የአንድነት ስሜታችን ብርታትና ቆራጥነት ስጥቶን፣ ያን ሁሉ የመከራ ዘመን አሳልፈን እንደገና ለመገናኘት እንድንበቃ፣ የተባበሩት መንግሥታት የሚቀይስልንን መንገድና የሚከፍትልንን አዲስ ምዕራፍ የምንቀበለው፣ ወሰን በሌለው ደስታና ጽኑ በሆነ ተስፋ ነው:: ፍቅራችንና ሕብረታችን መሣሪያ ሆኖን፣ የምናደርገው ጥረትና የምናመርተው ውጤት፣ በዚህ በተስቃየ ዓለም ውስጥ

ለሚኖሩት ወገኖቻችን፣ ምሳሌነታችን ይጠቅም ይሆናል ብዬ ከልብ የማደርገውን ተስፋ ሳልጠቅሰው ማለፍ አልፈልግም።

...... በመጨረሻም ለመናገር የምፈልገው፣ በኤርትራ ውስጥ ስላሉት የጣልያን ዜጎችና የእነሱ ተወላጆች ጉዳይ ነው። ከዚህ ቀደም በየኮሚቴው ደጋግሜ እንደተናገርኩት፣ አሁንም ለጠቅላላው ጉባኤ የማረጋግጠው፣ በኤርትራ የሚኖሩት የጣልያን ዜጎችና ተወላጆቻቸው፣ የተባበሩት መንግሥታት በወሰነው መሠረት፣ መብታቸው የሚከበርላቸውና ነፃነታቸው የሚጠበቅላቸው መሆኑን ነው። ይህን በመሰለው ጉዳይ፣ ከፍ ያሉት ገዢዎቹ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጠላትን ድል አድርገው አገራቸው በገቡበት ዕለት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማጥቃት ተልከው የመጡት የጣልያን ዜጎችና ተወላጆቻቸው በሙሉ፣ ደህንነታቸው እንዲጠበቅና የሠላም ሕይወታቸው እንዲቀጥል የሰጡትን አዋጅና የፈጸሙትን ሰብዓዊ ተግባር፣ የዓለም ታዛቢዎችና በተለይም የጣልያን ሕዝቦች ምንጊዜም የሚዘነጉት አይመስለኝም። ...... ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት ሁሉ፣ ለሰው ልጅ የሚሰጠው መብትና ነፃነት ለሁሉም በእኩል ደረጃ መከበር እንዳለበት፣ የኢትዮጵያ መሠረታዊ አቋምና ዓላማ ስለሆነ፣ የትናንት ጠላት የዛሬ ወዳጅ እየተባለ፣ የሚፈጸም አድሎና ጥቃት እንደማይኖር ዋስትና መስጠት እፈልጋለሁ።

የተከበሩ ሊቀመንበር፤

..... ለንግግሬ ማከተሚያ በአንድ ዓረፍተ ነገር ሀሳቤን ለማጠቃለል እንድችል ፈቃድዎን እጠይቃለሁ። ይኸውም፤ ለብዙ ዓመታት የቆየው፤ የስደትና የስቃይ ሕይወት ከተፈጸመ በኋላ፣ ኤርትራውያኖች ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር፣ አንድነታቸው ተመልሶላቸው፣ የጋራ ሕይወታቸውን የሚመሠርቱበት ዕድል የሚከፈተው፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅታችን ትክክለኛ ፍርድ ስለሆነ፣ አዲስ የምንከፍተው የታሪክ ምዕራፋችን ይህን ሁሉ አጉልቶ ለተከታዩ ትውልድ እንደሚያስተላልፍልን እምነቴ ጽኑ መሆኑን ነው .......

»

ከዚህ በላይ የተገለጸው የአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ንግግር፣ ለጠቅላላው ጉባኤ እንዲቀርብ በፕሮግራም የተመደበ አልነበረም። ለኤርትራ የተዘጋጀውን መፍትሔ፤ የአባል መንግሥታት እንደራሴዎች ድጋፋቸውን ሆነ ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ ከመጀመራቸው በፊት፤ ጉባኤው ስለሚሰጠው ውሳኔ፤ ባለጉዳዩ የሆኑት አቶ አክሊሉ በቅድሚያ አስተያየታቸውን በዚህ እኳኋን ዘርዝረው ለማቅረብ፤ የውስጥ ደንቡ አይፈቅድላቸውም ነበር። ከዚሁ የተነሣ፤ ሊቀመንበሩ የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሰጠው መግለጫ፤ « ...... ምንም እንኳ በውስጥ ደንባችን ለውሳኔ በቀረበልን ጉዳይ ላይ ንግግሩ ከመጀመሩ በፊት፤ የባለጉዳዩ አስተያየት በቅድሚያ እንዲቀርብ የተፈቀደ ወይም የተለመደ ባይሆንም፣ ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተብራርቶ የቀረበልንን ዋስትና የሚሰጥ ንግግር፣ ሁላችንም ያዳመጥነው በጋለ እና ጥልቅ በሆነ ስሜት መሆኑን ተረድቻለሁ። ....... በበኩሌም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አክሊሉ ንግግር፣ ደስ የሚያሰኝ በመሆኑና ለሥራችንም ጠቃሚ እንደሆነ በመገመት የውስጥ ደንባችንን መከተል አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም። ...... » ካለ በኋላ፤ የጉባኤው ሥራ እንዲቀጥል አደረገ። ጉባኤው ሥራውን እንደጀመረ ከስልሣዎቹ የመንግሥታት እንደራሴዎች መካከል የመጀመሪያው ተናጋሪ ሆኖ የቀረበው የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኛ ስለሆነ፤ ምን

አስተያየት እንደሚሰጥ ለመሰማት፣ በተለይ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ከፍ ያለ ጉጉት አድሮባቸው ነበር። እንደተፈራው አልሆነም። የእንግሊዝ መልዕክተኞች መሪ ሰር ፍራንክ ሶስኪስ፣ (SIR FRANK SOSKICE) በንግግሩ መግቢያ ላይ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሰጡትን መግለጫ ካመሰገነ በኋላ፣ የኤርትራ ጉዳይ ብዙ ምርምሮች የተካሄዱበት እና በተለይም በፖለቲካው ኮሚሲዮን በጥልቀት የተጠና ስለሆነ፣ ጠቅላላው ጉባኤ እንዲያጸድቀው የቀረበው መፍትሔ፣ ከፍተኛ የሆነ የድምፅ ድጋፍ ማግኘት ይገባዋል ሲል አስተያየቱን ገለጸ። ሰር ፍራንክ ሶስኪስ ንግግሩን በመቀጠል፣ ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል የቀረበውን ሀሳብ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚቀበለውና ጣልያንም ሊቃወመው እንደማይችል ከጠቀሰ በኋላ፣ ይህ መፍትሔ ፍሬያማ ውጤት ይሰጣል ተብሎ ከፍ ያለ ተስፋ የሚደረገው፣ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው አገሮች ብቻ ሳይሆን፣ ምሳሌነቱ ለአፍሪካ አገሮች ጭምር እንደሚሆን ታላቋ ብሪታንያ ያላትን ሙሉ ዕምነት ለጠቅላላው ጉባኤ አስረድቷል።

የአምስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ዝግጅት ሲደረግ፣ እንግሊዞች ለኢትዮጵያ የሚሰጡትን ድጋፍ በማቀዝቀዛቸው ከዚህ ቀደም በጃንሆይና በመንግሥታቸው ዘንድ ሥጋት አድሮ እንደነበረ ይታወሳል። የዚህም ዋና ምክንያት፣ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን፣ እንግሊዞች አጥብቀው የሚፈልጉትን የአቆርዳትን አውራጃ ወደ ሱዳን ማቀላቀል ጉዳይ፣ የኤርትራ ሕዝብ በሙሉ ይቃወማል ሲል ያቀረበው ራፖር ስለአበሳጫቸው መሆኑ ታውቋል። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም የእንግሊዞች ድጋፍ መቀዝቀዙ ሲነገራቸው፣ እራሳቸው ወደ ሎንዶን ሄደው የመንግሥቱን መሪዎች ለማነጋገር እስከ ማሰብ ደርሰው ነበር። ነገር ግን የመርማሪው ኮሚሲዮን ራፖር በጊዜያዊው ኮሚቴ በሚጠናበት ጊዜ እና ከዚያም በፖለቲካው ኮሚሲዮን የፌዴሬሽን መፍትሔ ሲዘጋጅ፣ እንግሊዞች ምንም እንኳ ከአሜሪካኖች ጋር ሆነው የሞቀ እርዳታ ሲሰጡ ባይታዩም፣ የተቃውሞ ሀሳብ ባለመስጠታቸው፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እና በመንግሥታቸው ላይ ያደረው ሥጋት እየቀነሰ ሄደ።

አቶ አክሊሉ ለንጉሠ ነገሥቱ ካቀረቡት ማስታወሻ ለመረዳት እንደተቻለው፣ እንግሊዞች የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መቀላቀል ሲደግፉ የቆዩት፣ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነበር። የመጀመሪያው፣ « ታላቋ ሱማሌ » የሚባል ግዛት ለመፍጠር የኦጋዴንን አውራጃ ቆርጦ ለመውሰድ በመፈለጋቸው፣ ለማካካሻ የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ እንደግፋለን አሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ የታላቋ ሱማሌ መፈጠር ጉዳይ እንደማይሳካ ሲያውቁት፣ ከኤርትራ ግዛት የምዕራባዊው ቆላ አውራጃ ወደ ሱዳን እንዲከለልና ሌላው ግዛት ከኢትዮጵያ ጋር እንዲሆን ለሁለት ዓመታት ያለማቋረጥ ታገሉ። እሁን በመጨረሻው፣ እነሱ ያቀዱት ሀሳብ ሁሉ እንዳም የማይፈጸም መሆኑን አውቀው ተስፋ ሲቆርጡ፣ የመላ ኤርትራን ግዛት በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ማቀላቀል፣ ምንም እንኳ ፊት ለፊት መቃወም ባይፈልጉም እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ፣ እንደ አሜሪካና እንደ አንዳንድ መንግሥታቶች ድጋፋቸውን በሞቀ መንፈስ መስጠት አልፈለጉም።

የአንድ አገር የፖለቲካ አቋም በጥቅም ምክንያት እንደ አየር ጠባይ ተለዋዋጭ በመሆኑ፣ ወደ ኋላ ተመልሶ የነበረውን ማስታወስና ከዛሬው ሁኔታ ጋር ማገናዘብ ጠቃሚ ይሆናል። ኤርትራ ወደ ጥንት እገሯ እንድትመለስ ኢትዮጵያ ያቀረበችው ማመልከቻ፣ በመስከረም 1945 ዓ.ም ሎንዶን ላይ በተደረገው የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ በሚታይበት ጊዜ፣ ጥያቄው ተገቢነት

ስለሌለው፣ ከምክር ቤቱ አዠንዳ ላይ እንዲሰረዝ ፈረንሣይ፣ መስኮብና አሜሪካ ስለሌለው፣ ከምክር ቤቱ አዠንዳ ላይ እንዲሰረዝ ፈረንሣይ፣ መስኮብና አሜሪካ የውሳኔ ሀሳብ ሲሰጡ፤ ኤርትራ ያለ ኢትዮጵያ ሕይወት ስለማይኖራት፣ ጉዳዩ በጥልቅ መመርመር አለበት ብሎ ከመሰረዝ ያዳነው፣ የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኧርኔስት ቤቨን ነበር። ከዚያም በኋላ ለብዙ ዓመታት፤ ጣልያን በምንም ምክንያት ወደ ኤርትራ መመለስ የለበትም ብሎ በማገድ እና ከምዕራብ ቆላ አውራጃ በስተቀር ሌላው ግዛት ሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሐድ፤ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ያሳየው አቋም፣ ለኢትዮጵያ ድጋፍ መሆኑ አይካድም። አሁን ደግሞ በ1950 ዓ.ም መጨረሻ ላይ፣ እንግሊዞች ኢትዮጵያን የመርዳት ፍላጐታቸው የተዳከመበት ምክንያት ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን፣ አሜሪካኖች ደግሞ ከተጠበቀው በላይ ድጋፋቸውን ያጋሉት ለምንድን ነው ? የሚል ጥያቄ ቀርቦ ነበር።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዲን አቸሰን ራሱ በየኮሚቴው እየተገኘ፣ የቀረበው መፍትሔ እንዲጸድቅ ያን ሁሉ ጥረት ያደረገው፣ ዩናይትድ ስቴትስ በአሥመራ ላይ ያቋቋመው « ራዲዮ ማሪና » የተባለው የመገናኛ ማዕከል፤ ያለአንዳች እንቅፋት ለመቀጠል እንዲችል ከኢትዮጵያ መንግሥት ዋስትና ስለተሰጠው ነው ሲሉ፤ አንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች ተችተዋል። በእርግጥ « ራዲዮ ማሪና » (ኋላ ቃኘው ሻለቃ) የተባለው የመገናኛዎች ድርጅት፤ ለአሜሪካኖች አጅግ ጠቃሚያቸውና አስፈላጊያቸው መሆኑ አይካድም። ይሁን እንጂ በዚያን ዘመን እንደነበረው የፖለቲካ ሂደት፣ ኤርትራ ነፃ ትውጣ ! ወይም ከነፃነት በፊት ጣልያን ለአሥር ዓመታት በሞግዚትነት ያደራጃት ! ተብሎ ቢወሰን እንኳ፤ ለራዲዮ ማሪና እንቅስቃሴ አሜሪካንን ደፍሮ እንቅፋት ለመፍጠር የሚሞክር እንደማይኖር የታመነ ነው። ከጦርነቱ በኋላ፤ አሜሪካኖች ቀስ በቀስ ወደ ኢትዮጵያ እየተጠጉ፣ የአገሪቱን ጠቅላላ ሁኔታ ሲያጠኑ፣ ከነፃነት በኋላ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት በእንግሊዞች ምን ያህል እንደተሰቃየ፣ ከዚህም ሌላ ጣልያን ወደ ኤርትራ ተመልሶ ጉረቤት ቢሆን፣ ንጉሠ ነገሥቱ የስጉበትን ምክንያት ተረድተው፣ ይህችን ችግረኛ አገር ቢያንስ በሞራል ለመርዳት ሳያስቡ እንዳልቀሩ ማመን ይቻላል። እንደዚሁም፤ ኢትዮጵያ፣ ኤርትራን በፌዴሬሽን አስተዳደር እንድትቀበል ሲደግፉ፣ ለራዲዮ ማሪና ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፤ በቀይ ባሕር አካባቢ አገሮች ሠላምና ደህንነት ተመስርቶ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ጥቅም ይጠበቃል ብለው ማሰባቸው የማይጠረጠር ነው።

አሜሪካኖች፤ አሥራ አራት አገሮችን አሠልፈው ያዘጋጁት መፍትሔ በፖለቲካው ኮሚሲዮን ድል ያገኘ ቢሆንም፤ ጉዳዩ ለጠቅላላው ጉባኤ ሲቀርብ፣ ከስልሣ (60) የመንግሥታት እንደራሴዎች መካከል፣ በዩናይትድ ስቴትስ ድጋፍና እርዳታ ብቻ ሊጸድቅ ይችላል ብላ ኢትዮጵያ አልጠበቀችም። ጠቅላላው ጉባኤ ለሚያደርገው ውሳኔ፣ የአንድ መንግሥት እንደራሴ አቅም አንድ ድምፅ ብቻ ስለሆነ፤ የፌዴሬሽኑን መፍትሔ ለማጽደቅ፤ ከሌላው አባል አገሮች ሁለት ሶስተኛ የሆነው የድጋፍ ድምፅ ያስፈልግ ነበር። ጉባኤው እንደተከፈተ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በቅድሚያ የሰጡት ሰፊ ማብራሪያ፣ ስለ ፌዴሬሽኑ ሕግ መከበር ከኢትዮጵያ የሚፈለገውን ዋስትና የሚያረጋግጥ በመሆኑ፤ የብዙዎች አገሮችን መልካም አስተያየት ማርኳል።

የቻይና መልዕክተኞች መሪ ሚስተር ሱን ቺ ዩ (TSUNE CHI YU) ድጋፉን ከመስጠቱ በፊት ለጉባኤ በገለጸው አስተያየት፤ « ..... የኢትዮጵያ የውጭ

ጉዳይ ሚኒስትር፣ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር በተግባር ላይ እንዴት እንደሚውል፤ አግባቢና እስተማማኝ የሆነ ዋስትና ያለው መግለጫ በሰጠን ጊዜ፣ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በመካከላችን ተገኝቶ አዳምጦት ቢሆን ኖሮ፣ ሙሉ በሙሉ ተስማምቶ በተመሳሳይ አነጋገር ትብብሩን ይገልጽልን ነበር ብዬ አስባለሁ ...... » ብሏል:: እንደዚሁም የሊባኖስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር አሙን (AMMOUN) ባደረገው ንግግር፤ « አክሊሉ ሀብተወልድ በኢትዮጵያና በንጉሠ ነገሥቱ ስም ሆነ፣ ፌዴሬሽኑ በተግባር ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በሰፊው የገለጹልን መሠረታዊ ጉዳይ፤ ሁላችንንም ስለአረካን፣ የሊባኖስ መንግሥት ለቀረበው መፍትሔ ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል» ካለ በኋላ፤ « ...... የታወቁትና የተከበሩት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት፣ በዘመናቸው ለነፃነትና ለትክክለኛ ፍርድ የተሰዉ እና፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም፣ ዓላማውንና ግቡን እንዲፈጽም ጥረታቸውን ያላጓደሉ ስለሆኑ፣ ጉባኤያችን ለኤርትራ አስተዳደር የሚሰጠው ውሳኔ፣ በተግባር ላይ እንደሚገለጽ ዕምነታችን የተሟላ ነው ...፣.. » ብሏል::

ከየመንግሥታቱ እንደራሴዎች ይህን በመሰለ መልክ ከተገለጹት አቋሞች ውስጥ፣ ከሁሉም ይበልጥ አስደናቂ ሆኖ የታየው፣ የፌዴሬሽኑን መፍትሔ ለመቃወም ተዘጋጅቶ የመጣው የኢራቅ መልዕክተኛ ሚስተር ሞሐመድ ፋድሒል ዡማሊ (M.FADHIL JAMALI) ሀሳቡን ለውጦ ደጋፊ ሆኖ መገኘቱ ነው:: አል ዡማሊ፣ ስለወሰደው አቋም ለጉባኤው ሲያስረዳ፤
« ...... የፌዴሬሽኑ አስተዳደር በትክክል በተግባር ላይ እንደሚፈጸምና፣ ከዚህም በላይ በኤርትራ ያሉት እስላሞች እንደ ክርስቲያኖቹና እንደሌሎቹ ሁሉ፣ የእኩልነት መብታቸውና ነፃነታቸው የሚጠበቅላቸው መሆኑን፣ ከኢትዮጵያ የተሰጠው ዋስትና የሚበቃ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: ....... ከዚህም በቀር የጉባኤውን ሥራ ለመከታተል ኒውዮርክ የመጣው የኤርትራ የእስላሞች ሊግ መሪ፣ ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በተሰጠው መግለጫ መደሰቱን ገልጾልኛል:: እንደዚሁም፤ በኢትዮጵያና በኤርትራ የሚኖሩት እስላሞችና የዓረብ ተወላጆች ሁሉ፣ የታሰበውን የፌዴሬሽን መፍትሔ የሚቀበሉት መሆኑን ሰምቻለሁ:: በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች፣ ከዚህ በፊት ለፖለቲካው ኮሚሲዮን አቅርቤው የነበረውንና አሁንም በጠቅላላው ጉባኤ እንዲታይልኝ ያዘጋጀሁትን ረቂቅ ውሳኔ ሰርዤ፤ በአስራ አራት አገሮች ተቀነባብሮ በፖለቲካው ኮሚሲዮን ተቀባይነት ካገኘ በኋላ፣ ጉባኤያችን እንዲያጸድቀው የተጠየቀውን የፌዴሬሽን መፍትሔ ለመደገፍ ወስኛለሁ ...... » አለ:: የኢራቅ መልዕክተኛ ከዚህ ቀደም ለፖለቲካው ኮሚሲዮን አቅርቦት ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረውና አሁንም ጠቅላላው ጉባኤ እንዲያይለት አዘጋጅቶት የነበረው ረቂቅ ውሳኔ፤ « ...... የኤርትራ ሕዝብ ነፃነትን ከማግኘትና በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ከመቀላቀል፤ የትኛውን እንደሚመርጥ በሬፈራንዶም መጠየቅ አለበት ..... » የሚል ሀሳብ ነበር::

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሁሉ፣ ጠቅላላው ጉባኤ ስለ ኤርትራ ጉዳይ ለውሳኔ በቀረበለት መፍትሔ ላይ መነጋገር ከመጀመሩ በፊት፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ለመላው የተባበሩት መንግሥታት እንደራሴዎች የሰጡት የዋስትና ቃል፣ በብዙዎቹ መልዕክተኞች ላይ የነበረውን ጥርጣሬ ለማስወገድና ብዙ ደጋፊዎች ለማፍራት ችሏል:: የተባበሩት መንግሥታት በሚያጸድቀው የፌዴራል አክት መሠረት፣ መብትና ነፃነት ለሁሉም ወገን በእኩል ደረጃ እንዲከበር፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት እንከን በሌለው ሥርዓት በተግባር ላይ ያውለዋል ሲሉ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የሰጡት ማረጋገጫ፣ ከሰልሣዎቹ አባል መንግሥታት መካከል፣



ታኅሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ የተባበሩት መንግሥታት ሲወስን፣ ለአክሊሉ ሀብተወልድ የመጨረሻ እፎይታ ነበር።

(ኒውዮርክ ታህሣሥ 1950)

የአርባ ስድስቱን አገሮች ዕምነትና ሙሉ ድጋፍ አስገኝቷል። ጉባኤው እንደተከፈተ ክርክሩ ሳይጀመር፣ አቶ አክሊሉ ይህን በመሰለ መልክ ከኢትዮጵያ የሚፈለገውን ዋስትና አስፋፍተውና አብራርተው ባያቀርቡት ኖሮ፣ በአፈጻጸሙ ላይ ኢትዮጵያ ለግዴታዎቿ የምትሰጠው ዋስትና እንዴት ነው ? እያሉ የጠላት ወገኖች በሚያጉርፏት ጥያቄዎች፣ ጉዳዩን ለማወሳሰብና ውሳኔውን ለማዘግየት ይችሉ ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ መሪ፣ ባላቸው ሰፊ ኤክስፔሪያንስ፣ ሳይቀደሙ በመቅደም፣ በድፍረት የወሰዱት እርምጃ፣ የተንኮለኞቹን ቅስም ከመስበሩም ሌላ፣ የጉባኤውን ሥራ ለማፋጠንና የመጨረሻውን ውጤት ለማሳመር ረድቷል።

ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም በቅዳሜ ምሽት፣ የአምስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ሊቀመንበር የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ናስሮላህ ኢንተዛም፣ (NASROLLAH ENTEZAM) ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል ከስልሣ (60) አባል መንግሥታቶች ውስጥ በአርባ ስድስት (46) ድምጽ ድጋፍ፣ መወሰኑን የሚያበስር የፍርድ ደወል ሲያሰማ፣ በስብሰባው አዳራሽ የተገለጸው ደስታና ጭብጨባ እጅግ የጋለ ነበር። ከአንድ ዓመት በፊት በ1949 ዓ.ም በተደረገው በአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ፣ ለውሳኔ በስሉ የቀረበው የኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ጉዳይ ተሰናክሉ፣ በድጋሚ መርማሪ ኮሚሽን እንዲያጣራ ካስወሰኑት የላቲን አሜሪካ አገሮች መካከል አስራ አራት መንግሥታት፣ (አርጀንቲና ጭምር) ለፌዴሬሽኑ መፍትሔ የድጋፍ ድምፃቸውን ሲሰጡ ማየት፣ ለኢትዮጵያ መልዕክተኞች እጅግ አስደናቂ ነበር። ከላቲኖቹ ውስጥ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መሆን የለባትም ብለው አሁንም በተቃዋሚነታቸው የቀጠሉት፣ ኩባ እና ጓቴማላ፣ ሳልቫዶር እና ዶሚኒከን ሪፐብሊክ በድምሩ አራት አገሮች ብቻ ሆኑ።

በሶስተኛውና በአራተኛው ጠቅላላ ስብሰባ ላይ የተካፈለው፣ የአርጀንቲና መልዕክተኛ ሆሴ አርሴ (JOSE ARCE) የጣልያን አሽከርነቱን በይፋ ያስታወቀና የአገሩንም ክብር ያዋረደ መሆኑ ስለተመሰከረበት፣ የፋሽስቱ የጄኔራል ፔሮን መንግሥት ለአምስተኛው ጉባኤ መልዕክተኛው አላደረገውም። በአራተኛው ጉባኤ ዘመን ሆሴ አርሴ ምንም እንኳ የኢትዮጵያን ጥያቄ በማሰናከል ድል አስገኝቻለሁ ብሎ ከጣልያን ጋር ቢፎክርም፣ የሊቢያ የወደፊት ነፃነት በተወሰነ ጊዜ፣ ሕገ መንግሥቱን ለማዘጋጀት የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ሆኖ ለመመረጥ ያደረገው ጥረት አልተሳካለትም ነበር። የሆሴ አርሴ እጩ ኮሚሽነርነት የከሸፈበት ዋናው ምክንያት፣ ብዙዎቹ አባል አገሮች በኤርትራ ጉዳይ የኮሎኒያሊስት መሣሪያ ሆኖ ይፈጽመው የነበረውን አሳፋሪ ሥራ በማየት ድጋፋቸውን ስለነሱት ብቻ ሳይሆን፣ በአሽከርነት ከልቡ ያገለገለውም የሮማ መንግሥት፣ ለሊቢያ ሕገ መንግሥት አዘጋጅነት ከአርጀንቲናው ይልቅ የሆላንዱን መልዕክተኛ በመምረጡ ነበር። የኤርትራ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠበት በዚህ ስብሰባ ላይ፣ የአምባሳደር አርሴ ተካፋይ አለመሆን እና የአርጀንቲና መንግሥት ደጋፊነት፣ ኢትዮጵያ የምትጠብቀው አልነበረም።

ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም የአምስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትዋሀድ እጅግ ከፍ ባለ ድምፅ ብልጫ ሲያጸድቅ፣ ስለ ፌዴሬሽኑ አስተዳደርና የሥልጣን ድርሻ፣ በሰጠው ዝርዝር ውሳኔ ውስጥ (RESLOUTION N 390V) መሠረታዊ የሆኑት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

1. ኤርትራ፤ በንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ሥር ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ተቀላቅላ የራሷ የሆነ የውስጥ አስተዳደር መንግሥት ታቋቁማለች።

2. የፌዴራሉ መንግሥት የሆነችው ኢትዮጵያ፣ በመከላከያ እና በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ በአገር ውስጥ እና በውጭ ንግድ ጉዳይ፣ በአገር ውስጥ እና በውጭ መገናኛዎች፣ በፋይናንስ እና በባሕር ወደቦች አስተዳደር ሙሉ ሥልጣን ይኖራታል። እንዲሁም የፌዴሬሽኑን የግዛት ክልል ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነትና ሥልጣን፣ የፌዴራሉ መንግሥት ድርሻ ስለሆነ፣ ለዚህ ተግባርና አገልግሎት የሚያስፈልገውን ወጭ ለመሸፈን በመላው የኤርትራ ግዛት የፌዴራል ታክስ ይታወጃል።

3. የኤርትራ የውስጥ አስተዳደር ደግሞ፣ የፌዴራሉ መንግሥት ለሆነው ለኢትዮጵያ ከተዘረዘሩት የኃላፊነት ድርሻዎች ውጭ የሆኑትን ጠቅላላ ጉዳዮች፣ በሙሉ ሥልጣን ያከናውናል። እንደዚሁም ለውስጥ አስተዳደር አገልግሎት የሚውል ታክስና ግብር የመተመንና የማስከፈል፣ የውስጥ አድሚኒስትሬሽኑን በጀት የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል። ለኤርትራ የውስጥ አስተዳደር፣ በሕዝብ የተመረጡ መማክርቶች የሚመደቡበት የሕግ አውጭ ምክር ቤት የሚመሠረት ከመሆኑም በላይ፤ ለመንግሥቱ አመራር ከፓርለማው ኃላፊነትና ሥልጣን የሚቀበለው የሕግ አስፈጻሚ ክፍል እና የፍትሕ አካላት ይቋቋማሉ።

4. እነዚህን መሠረታዊ ነጥቦች ተመርኩዞ በተባበሩት መንግሥታት የሚመረጠው « ኮሚሽነር » የኤርትራን መተዳደሪያ ሕገ መንግሥት ያዘጋጃል።

5. በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር የሚዘጋጀው ሕገ መንግሥት፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠንቶ ከተወሰነ በኋላ፣ በንጉሠ ነገሥቱ ጸድቆ በሥራ ላይ እስከሚውልበት እስከ መስከረም 15 ቀን 1952 ዓ.ም ድረስ፣ በኤርትራ ያለው የታላቋ ብሪታንያ ወታደራዊ አስተዳደር በሥልጣን ይቆያል።

## ደስታና ቅሬታ

የፌዴሬሽን ሥርዓት ትርጉሙና ግብሩ በትክክል ተብራርቶ በማይታወቅበት ዓለም፣ የተባበሩት መንግሥታት የሰጠውን ውሳኔ ለማክበር ቃል ገብቶ ከመቀበል በስተቀር፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና መንግሥታቸው ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም።

በኒውዮርክ ስለተደረገው ውሳኔ፣ በንጉሠ ነገሥቱ አካባቢ ያሉት መሳፍንትና መኳንንት ደስታና ቅሬታ በተዋሀደው መንፈስ አስተያየታቸውን ቢገልጡም፣ ከሁሉ ያበልጥ ንጉሠ ነገሥቱን ያሳሰባቸው፣ ኤርትራ ወደ እናት አገሯ የምትመለሰው ያለአንዳች ውል መሆን አለበት ብለው፣ ለብዙ ዓመታት ሲዋጉ የኖሩት ኤርትራውያን የአንድነት ወገኖች፣ የተገኘው ፍርድ የሚጠቅመን እንጂ የሚጎዳን አለመሆኑን ተረድተው በደስታ መንፈስ እንዲቀበሉት ማድረግ ነበር። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ባላቸው የመከበርና የመፈራት ኃይል፣ የፌዴሬሽኑን

ውሳኔ ተቀብለነዋል በማለት ፋንታ አልተቀበልነውም ቢሉ ኖሮ፣ የአንድነት ወገኖች በደም ፍላት ሕዝቡን አነሳስተው፣ ከማን ጋር እንደሚዋጉ በትክክል ባይታወቅም፣ ለጦርነቱ ከመዘጋጀት አይመለሱም ነበር።

የፌዴሬሽኑ መፍትሔ እንደሚጸድቅ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ቀደም አድርገው የሚያውቁት ስለሆነ፣ በማህበረ ፍቅሪ ሀገር ያሉት ዋና ዋና የአንድነት መሪዎች፣ የፍርዱን አካሄድ እንዲገነዘቡት፣ ከታማኞቻቸው አንዱ የሆኑትን አስፍሐ ወልደሚካኤልን በአፈጉባኤነት ወደ ኤርትራ ልከው ስለነበረ፣ የኒውዮርኩ የመጨረሻ ውሳኔ አሥመራ በተሰማ ጊዜ፣ እንደተፈራው አልሆነም። በእርግጥ፣ የአንድነት ወገኖች፣ የጠየቅነው ተሟልቶ አልተፈረደልንም በማለት ያደረባቸውን ቅሬታ ባይሸሽጉም፣ የንጉሠ ነገሥቱን መሪ ትዕዛዝ በአክብሮት ተቀብለው ስለተሰጠው ውሳኔ የኤርትራ ሕዝብ ደስታውን እንዲገልጥ ከማስደረግ ችላ አላሉም። የታወቁት ያገር ፍቅር አንድነት መሪዎች፤ ራስ ኪዳነማርያም ገብረመስቀል፣ ደጃዝማች በየነ ባራኪ እና አቶ ተድላ ባይሩ፣ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በአስፍሐ በኩል ባቀረቡት ልዩ መልዕክት፣ የገለጹት አስተያየት የሚከተለው ነበር።

« ...... ታሪክና ትውልድ በሃምሳ ዓመታት የቅኝ ግዛት አስተዳደር አይደመሰስም። እኛ ኤርትራውያን ጥንትም ሆነ ዛሬ፣ ነገም ሆነ ወደፊትም፣ ኢትዮጵያዊነታችንን የሚፍቀው የለም። ይህንንም ለተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን፣ ከዚያም በፊት ለአራቱ ኃያላን መንግሥታት መልዕክተኞች አስረድተናል። እነሱም ለገለጽነው ሀሳብና ላሳየነው መንፈስ ምሥክሮቻችን ናቸው። ነገር ግን አሁን የመጨረሻ ፍርዳቸው እንደተነገረን፣ ከእኛ የተገለጸው ሀሳብና የልብ ስሜት ሙሉ በሙሉ አልተደመጠልንም። የዓለም ታላላቆች የሚባሉትና
የዓለም ማህበር ዳኞች ሆነው የተሰየሙት፤ የሚሠሩት ሁሉ የዳኝነት ነገር አለመሆኑን፣ በሚገባ ተመልክተን ታዝበናቸዋል።

....... እኛ ኤርትራውያኖች በታሪካችን፣ በዘራችን ሆነ በባሕላችን፣ ለኢትዮጵያዊነታችን ጥያቄ አይቀርብበትም ብለን ስናረጋግጥ፤ ኢትዮጵያዊነታችሁ ከአንድ ሁለቴ መመርመር አለበት የተባለውን ውሳኔ ተቀብለን፣ በሚገባ አስረዳን። በሚገባም አረጋግጠን ስሜታችንን ገለጥን። ...... አሁን ደግሞ፣ እኛ የምንጠይቀው በእናት አገራችን እና በንጉሠ ነገሥታችን ጥላ ሥር መጠቃለል ነው ብለን ስናመለክት፤ የለም ከእናታችሁ ጋር ብትሆኑም ለየት ባለ አኳኋን ማደር ያስፈልጋችኋል ተባልን። ይኸ ሁሉ የሚደረገው በጠላቶቻችን ተንኮል መሆኑን ደህና አድርገን ደርሰንበታል። በእኛ በኤርትራውያን ዜጐችዎ እምነትና ሀሳብ ቢሆን ኖሮ፤ ለአገራችንና ለሕይወቷ የሚጠቅማትን ለመምረጥ፣ ከእኛ ከልጆቿ በስተቀር የማንንም የባዕድ አገር ዳኛ አንቀበልም ብለን፣ ሁላችንም ወደ ዘመቻ እናመራ ነበር። ነገር ግን የግርማዊነትዎ ኃላፊነት ለኛ ለታማኝ ዜጐችዎ ብቻ ሳይወሰን፣ ለዓለም ሠላም ደህንነት ጭምር በመሆኑ፣ እኛ የምንከተለው፣ ከርስዎ ከምንወድዎ ንጉሠ ነገሥታችንና ጌታችን የሚሰጠንን ትዕዛዝ እንጂ፣ የራሳችንን ስሜት መሆን የለበትም ብለን ወስነናል። ...... አሁንም ጃንሆይ መላክተኛዎን አቶ አስፍሐን ልከው፣ ጉዳዩን በተዘረዘረ ሁኔታ እንድንረዳውና፣ የተወሰነውንም እንድናከብር፣ የሰጡንን ትዕዛዝ በታላቅ ደስታ ተቀብለን፣ ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ሆነን እቀድሞው ቦታችንና ታሪካችን መመለሳችንን፤ የሚያበስርልንን ታላቅ በዓል በከፍተኛ ናፍቆት እንጠብቃለን ....... »

የተባበሩት መንግሥታት የሰጠውን ይህን ፌዴሬሽን የተባለ የአስተዳደር ውሳኔ፣ ባለጉዳዮቹ ኤርትራውያኖች በምን ስሜትና በምን መልክ እንደሚቀበሉት አሳሳቢ ሆኖ ስለነበረ፣ ጃንሆይ ቀደም አድርገው ለአስፍሐ ወልደሚካኤል የሰጡት ሚሲዮን ከዚህ በላይ በተገለጸው አኳኋን በጥሩ ሁኔታ በመከናወኑ በጣም ደስ ብሏቸዋል።

ከኒውዮርክ የኢትዮጵያ መልእክተኞች መሪ ለንጉሠ ነገሥቱ ባስተላለፉት ቴሌግራም፣ የተባበሩት መንግሥታት ያደረገው ውሳኔ ታሪካዊነት ያለውና የሚያስደስት ቢሆንም፣ የፌዴሬሽኑን አስተዳደር በተግባር ላይ ለማዋል፣ ጊዜ የሚጠይቁ ዝርዝር ሥራዎች መኖራቸውን አስረድተዋል።

*« ...... በዛሬው ምሽት (ትናንት ታኅሣሥ 2 ቀን) የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ፣ ኤርትራ በግርማዊነትዎ ዘውድ ሥር በፌዴራሲዮን እንድትቀላቀል፣ ከሰላሣ አባል መንግሥታቶች መካከል በአርባ ስድስት ድምፅ ብልጫ ውሳኔውን ሰጥቷል። ለብዙ ዓመታት በግርማዊነትዎ መሪነት ብርቱ ድካም የተደረገበት የኤርትራ ጉዳይ፣ የመጨረሻውን ውሳኔ ማግኘቱ የሚያስደስት መሆኑን የምገልጸው በልዩ ስሜት ነው። በድምፅ አሰጣጥ ላይ እንደታየው፣ የተቃወሙን አገሮች በድምር አሥር ብቻ ሲሆኑ፣ አብስታንሲዮን (ABSTANTION) ያደረጉት ደግሞ አራት አገሮች ናቸው። ከነዚህም ከአራቱ መካከል የስዊድንና የሳውዲ ዓረቢያ አገሮች መገኘት የግርማዊነትዎን መልዕክተኞች አስገርሞናል። ሌሎቹ ሶቪየት ሕብረትና ተከታዮቹ፣ እንዲሁም ፓኪስታንና ጓቴማላ ተቃዋሚዎቻችን እንደሚሆኑ ስለጠበቅናቸው አላስደነቀንም። ሆኖም በጠቅላላው ሲታይ የተቃዋሚዎቻችን ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው ማለት ይቻላል። ...... ቀደም ብዬ ለግርማዊነትዎ ሁኔታውን እንደገለጽኩት፣ የተባበሩት መንግሥታት በሰጠው ውሳኔ መሠረት፣ የኤርትራ አዲሱ የፌዴራሲዮን አስተዳደር ከመጀመሩ በፊት፣ ለሚቀጥሉት አስራ ስምንት ወራቶች የሚጠብቁን ከፍተኛ ሥራዎች ይኖራሉ። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ፣ በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ተዘጋጅቶ በመጨረሻ ግርማዊነትዎ የሚያጸድቀው የኤርትራ ሕገ መንግሥት እና፣ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ጋር የሚደረገው የሥልጣን እርክክብ ስምምነት ነው።*

*ከዚህ ቀጥሎ ለግርማዊነትዎ የማመለክተው፣ ከእኔ ጋር የተመደቡት መልዕክተኞችዎ፣ ክቡር ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፤ ክቡር አቶ አበበ ረታ፣ ክቡር ብላታ ዳዊት ዕቁበእግዚእ፣ አቶ ገብረመስቀል ክፍለእግዚእ፣ አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ፣ ልጅ እምሩ ዘለቀ፣ አማካሪያችን ሚስተር ጆን ስፔንሰር ያለ ዕረፍት ያደረጉትን ድካም ጃንሆይ እንዲያውቁላቸው እለምናለሁ። ....... በተጨማሪም ለግርማዊነትዎ የምገልጸው፣ የኤርትራ ጉዳይ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ፣ በድንገተኛ ሞት እስከተለዩን እስከ አለፈው ዓመት ድረስ፣ ክቡር አቶ ተስፋዬ ተገኝ ቢፖረል የግርማዊነትዎ ሚኒስትር፣ የሰጡትን ከፍተኛ አገልግሎት እዚህ ያለነው መልዕክተኞችዎ ጥልቅ በሆነ የሀዘን ስሜት የምናስታውሳቸው መሆኑን ነው። ...... በመጨረሻም ሳልጠቅሰው ለማለፍ የማልፈልገው፣ የኤርትራ ጉዳይ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ምክር ቤት በፍርድ እንዲታይልን በምንጥርበት ጊዜ፣ በ1946 ዓ.ም በፓሪስ የሠላም ጉባኤ ላይ ተካፋይ የነበሩት፣ ክቡር ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታእዛዝ በሞስኮ የግርማዊነትዎ ሚኒስትር፤ በስብሰባው ላይ ለጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ለደጋስፐሪ የሰጡትን ታሪካዊ መልስ እና፤ ያሳዩትን እጅግ የሚያኮራ የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ለምንጊዜውም የማንረሣው መሆኑን ነው። በ1936 ዓ.ም ግርማዊነትዎ በጀኔቭ የመንግሥታት ማህበር ትሪቡን ላይ ተገኝተው በአገርዎ በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጸመውን የፋሽስት ግፍ ለመላው ዓለም በሚናገሩበት ሰዓት፤ በአዳራሹ የነበሩት የጣልያን ፋሽስቶች ስለፈጸሙት ብልግና እና፣ ታላላቅ መንግሥታቶችም ስለአሳዩት ግዴለሽነት፤ ብላታ ሎሬንሶ የዓይን ምሥክርነታቸውን ለጉባኤው ሲያስረዱ፤ ያልተደነቀና ያላዘነ አልነበረም። ...... በዚህ እጅግ አስቸጋሪ በሆነው እና የብዙ ዓመታት ድካም በጠየቀው በኤርትራ ጉዳይ፣ በማናቸውም መስክ አገልግሎት ያበረከቱትን እና የረዱትን ሁሉ ከእኔ ይበልጥ*

ጃንሆይ ዝርዝር ስለሚያውቋቸው፣ የእኔ አስታዋሽነት ይህን ያህል ይጠቅማል ብዬ አላምንም። አንዳንዱን ጉዳይ በዚህ ቴሌግራም ለመጥቀስ የተገደድኩትም ትዝታዬ እየተቀሰቀሰ ስለአስቸገረኝ ብቻ ነው። ...... በዛሬው ዕለት በበኩሌ ትልቅ ደስታ እና እርካታ የሚሰማኝ፣ ለአገራችን ለኢትዮጵያ ታሪክ ግርማዊነትዎ የጣሉብኝን ሰምነት እንደታሰበውም ያህል ባይሆንም፣ የተቻለውን የመፈጸም ዕድል ስለአጋጠመኝ ነው ...... »

የግርማዊነትዎ አገልጋይ
አክሊሉ ሀብተወልድ

---

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለጃንሆይ በላኩት ቴሌግራም እንደገለጹት፣ የኤርትራን ፌዴሬሽን ሕገ መንግሥት የሚያዘጋጀው እና፣ ከዚያም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወስኖ በንጉሠ ነገሥቱ እስኪጸድቅበት ጊዜ ድረስ፣ ሥልጣኑ ወይም ኃላፊነቱ የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር መሆኑ ታውቋል። ጃንሆይ፣ ፌዴሬሽኑን በተግባር ላይ ለማዋል ብዙ ውጣ ውረድ መኖሩን በቅሬታ ቢቀበሉትም፣ በመጨረሻው ሕገ መንግሥቱ የሚጸድቀውና የሚታወጀው፣ በንጉሠ ነገሥታዊ ፊርማቸው መሆኑ ተደጋግሞ ስለተገለጸላቸው፣ « ...... የእኛን መልክም ፈቃድ በቶሎ እንድንለጥ የተሾመው ኮሚሽነር በቶሎ መጥቶ ዝግጅቱ መፋጠን አለበት ...... » ከማለት በስተቀር ለጊዜው የተለየ ትእዛዝ አልሰጡም።

ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል በተባበሩት መንግሥታት ስለተወሰነ፣ ማክሰኞ ታኅሣሥ 5 ቀን 1950 ዓ.ም በመላ ኢትዮጵያ በዓል ሆኖ እንዲከበርና፣ በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ንጉሠ ነገሥቱ ለመላው ሕዝባቸው መግለጫ እንዲሰጡ ተደረገ። በዚያን ዘመን የአዲስ አበባ ራዲዮ፣ በሀገር ፍቅር ማህበር ድምፃዊ ተጫዋቾች አማካይነት ሰፋ ያለ የምሽት ፕሮግራም የሚያሰናዳው፣ በሳምንት ሶስት ጊዜ፣ ማክሰኞ፣ ሐሙስና ቅዳሜ ስለሆነ፣ ብዙ አድማጭ ባለበት ቀን፣ የማክሰኞውን በዓል ዜና ለሕዝቡ በዝርዝር ለማቅረብ ጥሩ አጋጣሚ አግኝቷል። በጋዜጠኞም በኩል በዚያን ዘመን የዕለት እትም አልነበረም። በየሳምንቱ ሮብ የሚወጣው ሰንደቅ ዓላማችን የተባለው ጋዜጣ የማክሰኞውን በዓል አሟልቶ ለማተም በቂ ጊዜ ስለሌለው፤ ዕድሉ በየሳምንቱ ቅዳሜ ለሚዘጋጀው ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሆኖ ነበር።

ማክሰኞ ታኅሣሥ 5 ቀን ከጠዋቱ በአራት ሰዓት ተኩል፣ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠር የአዲስ አበባ ሕዝብ በተሰበሰበበት ክብረ በዓል ላይ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ንግግራቸውን የከፈቱት፡«.... መላው ሕዝባችን እንደሚያውቀው፣ የኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ በዘመነ መንግሥታችን ያለ ማቋረጥ የደከምንበት ነው...... » በሚል ቃል ነበር። ጃንሆይ እንደተናገሩት ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ለብዙ ዘመናት በሰው ኃይልና በገንዘብ ወጪ ምን ያህል ከባድ ጥረት እንደተደረገ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ጉዳዩን በሚበቃ ያህል ተረድቶታል ማለት አይቻልም። ሆኖም ከስልሣ ዓመታት በፊት፣ በጠላታችን በጣልያን ተቆርጠው የተወሰዱብን የመረብ ምላሽ ኤርትራውያን ወንድሞቻችን ወደ ጥንት አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ እስካሁን አለመመለሳቸውን ያውቃል። የሀገር ፍቅር ማህበር ድምፃውያን በልዩ ልዩ ዜማዎችና ግጥሞች ተወዳጁ ንጉሠ ነገሥታችን፣ ወንድሞቻችን ኤርትራውያኖች እንዲመለሱልን በዓለም ሸንጎ ላይ ፍርድ አስገኙልን እያሉ፤ የሕዝቡን መንፈስ በራዲዮ ስለቀሰቀሱት፣ በዓሉ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን፣ በየጠቅላይ ግዛቱም በደመቀ ሁኔታ ተከበሯል።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ በገነተ ልዑል ቤተመንግሥታቸው ሰገነት ላይ ሆነው ለመላው የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች ማስረዳት የፈለጉት፣ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን ነበር። ይኸውም፤ 1ኛ/ ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ጉዳዩን በቀጥታ ራሳቸው እየመሩት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው አማካይነት በዓለም ጉባኤ ፊት የተደረገውን አስቸጋሪ ክርክር ሲሆን፤ 2ኛ/ በተባበሩት መንግሥት አሁን በመጨረሻ የተሰጠው ውሳኔ፣ ከኤርትራ ሕዝብ በጣም የሚበዛው ወገን ያለአንዳች ሁተታ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ለመሆን የገለጸውን ፍላጐትና፣ ኢትዮጵያም ያቀረበችውን ጥያቄ የሚያረካ አለመሆኑን ነው። ከዚህም አያይዘው ይህ ውሳኔ አጥጋቢ ስላልሆነ አንቀበልም ብንል፣ አርባ አምስት ዓመት በተሰፋ፤ አሥር ዓመት በትግል፤ ሲንገላቱ የቆዩትን ኤርትራውያን፣ ለኢትዮጵያዊነት ያላቸውን ናፍቆት ከማዘግየት በስተቀር ሌላ ጥቅም አለመኖሩን አስረድተዋል። ከዚህም በቀር፣ የተባበሩት መንግሥታት በወሰነው መሠረት፣ የኤርትራ መተዳደሪያ ደንብ በጥንቃቄ ተዘጋጅቶ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው በመልካም ፈቃዳቸው እስከሚያጸድቁት ድረስ፤ ብዙ የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች መኖራቸውን ከጠቀሱ በኋላ፣ በንግግራቸው ፍጻሜ ላይ፤ « ....... ኤርትራውያኖች ለራሳቸው ደህንነት ሲሉ፣ ወደፊት ያለባቸውን የጋራ ኃላፊነት እንዲያስተውሉና ይህም የዓለም መንግሥታት የሰጠው ውሳኔ፣ በተቻለ ፍጥነት ፍጻሜ እንዲያገኝ፣ የርስ በርስ ፍቅራቸውንና ሕብረታቸውን እንዲያጠነክሩ፣ አደራ እንላቸዋለን ...... » ብለዋል።

ንጉሠ ነገሥቱ ለመላው ሕዝባቸው ባደረጉት በዚህ ታላቅ ንግግር፣ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስ በተባበሩት መንግሥታት የተወሰነው፣ በፌዴሬሽን መሆኑን ጨርሶ አልጠቀሱም። በዚያን ጊዜ በራዲዮም ሆነ በየጋዜጦቹ የተገለጸው፣ ኤርትራ በንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ውስጥ ሆና እንድትተዳደር መወሰኑን ብቻ ነበር። የፌዴሬሽኑ ጉዳይ በይፋ የተገለጸው፤ የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር አሥመራ ላይ ትልቅ ቢሮ ከፍቶ የኤርትራን ሕገ መንግሥት ማዘጋጀት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው።

ማክሰኞ ታህሣሥ 5 ቀን 1950 ዓ.ም በአዲስ አበባና በመላው ኢትዮጵያ በተደረገው ትልቅ በዓል ላይ፤ በኤርትራ ጉዳይ ለብዙ ዓመታት ያለማቋረጥ የታገሉትና፣ በመጨረሻም የገጠሟቸውን ጠላቶች ሁሉ አሸንፈው ይህን ውጤት ያስገኙት፣ የንጉሠ ነገሥቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ በሕመም ምክንያት አዲስ አበባ ተገኝተው ተካፋይ ለመሆን ሳይችሉ ቀሩ። የኤርትራን ጉዳይ፣ አራቱ የዓለም ኃያላን አገሮች መወሰን አቅቷቸው፣ ዳኝነቱን ለተባበሩት መንግሥታት ካዛወሩበት ጊዜ ጀምሮ፣ የደረሰውን ፋታ ያልሰጠ እጅግ አስቸጋሪ ሙግት በድጋሚ መዘርዘር ባያስፈልግም፣ በተለይ የአምስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ሂደት፣ ለአክሊሉ ሀብተወልድ ከወሰን ያለፈ የመንፈስ ጭንቅ እና ሥቃይ የሰጠ መሆኑን መጥቀስ ይገባል። ጉዳዩ በጊዜያዊው ኮሚቴ መጠናት ከጀመረበት ቀን አንስቶ፣ በዋናው ኮሚሲዮን ሙሉ ድጋፍ ካገኘ በኋላ፣ ለጠቅላላው ጉባኤ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ እስከተሰጠበት ሰዓት ድረስ፣ ለአምስት ወራቶች የቀን ሠላም፣ የሌሊት እንቅልፍ አልነበራቸውም። ፍርድ የሚከናወነው በወገን ብዛትና በአድልዎ በሆነበት የዓለም ሸንጎ ላይ፣ የኢትዮጵያና የንጉሠ ነገሥቷ አደራ እየከበዳቸው፣ ያለማቋረጥ ለሶስት ዓመታት ከብዙ ጠላቶች ጋር የተጋፈጡት ሙግትና የተቀበሉት ሥቃይ፣ በምን ቀንና በምን ሰዓት ፍትሕ እንደሚያስገኝላቸው፣ አክሊሉ ሀብተወልድ መተንበይ አይችሉም ነበር።

-- በግንቦት 17 ቀን 1949 ዓ.ም በተደረገው በሰስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ፣ የኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ጉዳይ፣ እጅግ ከፍተኛ የሆነውን የአባል መንግሥታት ድጋፍ ካገኘ በኋላ፣ በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ላይ በጠላት ተንኮል ፍርዱ እንዳይጸድቅ በቀጠሮ ሲተላለፍባቸው፣

-- በህዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም በአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ደግሞ፣ ይኸው ለውሳኔ በሰሎ የነበረው የኤርትራ ጉዳይ፣ በጠላታችን በጣልያን እና በወገኖቹ ተንኮል ተሰናክሎ፣ እንደገና ምርመራ እንዲደረግ ያለአግባብ ሲፈረድባቸው፣ በኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ላይ የደረሰው ሰቀቀን እና ብስጭት ምን ያህል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል:: ከሁሉም ይበልጥ እጅግ አሳዛኝ የነበረው በዚህ በአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ዘመን የደረሰው ሁኔታ ነው:: ከዚያ እጅግ አድካሚና አስቸጋሪ ከነበረው ከላቲን አሜሪካ ጉዞ እና ዝግጅት በኋላ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ወደ ኒውዮርክ ለመሄድ ከአዲስ አበባ በተነሱ ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱ የተነገራቸው፣ « ...... ስለ ኤርትራ ዋና ጉዳያችን በጣልንብህ አደራ፣ በአሁኑ ስብሰባ ሲሆን ሲሆን ኤርትራን በሙሉ፣ ሳይሆን ደግሞ እንግሊዞች እንዳዘጋጁት በከፊሉ፣ አስፈርደህ በደህና ተመለስ ...... » የሚል ነበር:: የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ኒውዮርክ ከደረሱ በኋላ፣ የኤርትራ ጉዳይ በጠላት ተንኮል ተመርዞና ተወሳስቦ ሲያገኙት፣ ፍርድና እውነት በወገንና በገንዘብ መሸሸግ የለበትም ብለው ቢታገሉም፣ ዳኛ እና ረዳት ለማግኘት ሳይችሉ ቀሩ::

በዚያች በዕለተ ሰኞ ሕዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በአሥር ሰዓት፣ የአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ፣ ጣልያንና ወገኖቹ በቀየሱትና በፈለጉት መንገድ ውሳኔውን ሲሰጥ፣ በአክሊሉ ሀብተወልድ ላይ የደረሰውን ሀዘንና ምሬት መለካት የሚቻል አልነበረም:: ኤርትራ እንደገና እንድትመረመር፣ ዳኞቹም የኢትዮጵያ ወ ላቶች እነ ፓኪስታን እንደሆኑ፣ ሱማሌ ለጣልያን ተመልሳ እንድትሰጥ፣ የሚለው ይህ አሳዛኝ ውሳኔ ከጸደቀ በኋላ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መድረኩ ላይ ወጥተው፣ « ...... አገሬ ኢትዮጵያ በዓለም ሸንጐ ላይ ፍርድ ተነፍጓት ስታዝን ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም:: ....... በኤርትራም ሆነ በሱማሌ ጉዳይ ፍርዱን የሰጣችሁት ለግፈኛው ጣልያን ስለሆነ፣ «ዳቦ ለጠየቀ ድንጋይ» እንደተባለው፣ በደሉን የጣላችሁት በአገሬ በኢትዮጵያ ላይ መሆኑን እንድትረዱት እጠይቃለሁ ....... » ብለው፣ የስብሰባውን አዳራሽ ለቅቀው ሲወጡ፣ ተመልሰው የሚያዩት አልመሰላቸውም ነበር::

ይህ ሁሉ ከደረሰ ከአንድ ዓመት በኋላ፣ በታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም፣ ለብዙ ዓመታት የተጨነቁበትና የተንገላቱበት የኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ የመጨረሻውን ውሳኔ ሲያገኝ፣ እቶ አክሊሉና አብረዋቸው የደከሙት የኢትዮጵያ መልዕክተኞች፣ እርስ በርሳቸው ደስታቸውን የተገላለጹት፣ እንባ በተናነቀው ስሜት ነበር:: ብዙ ጊዜ ትዕግሥትና ጥንካሬ ከብልህነት ጋር ሲተባበሩ፣ በመጨረሻው ፍሬያማ ስለሚሆኑ፣ በአምስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስ ፍርድ ሲሰጥ፣ በአገራችን ታሪክ ላይ አንድ አዲስ ምዕራፍ ተከፍቶ በኢትዮጵያ ሰማይ የደስታ ፀሐይ ስታሽበርቅ ታየቻቸው:: ከዚህ መልካም ውጤት በኋላ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ ወደ አገራቸው ተመልሰው፣ ከንጉሠ ነገሥቱ የተዘጋጀላቸውን ልዩ ሽልማትና፣ አድናቆትን የተመላ ምሥጋና ተቀብለው በመደሰት ፋንታ፣ ለብዙ ጊዜ በአእምሮአቸውና በሰውነታቸው ላይ ሲከማች የቆየው ጭንቀትና ድካም ጤናቸውን ስለአወከው፣ ሥራቸውን ሲጨርሱ ወደ ሆስፒታል ማምራት ግዴታ ሆነባቸው::

የኤርትራና የኢትዮጵያ መቀላቀል እንደተወሰነ፣ ከአዲስ አበባ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ ግርማዊት እቴጌ ጭምር፣ ለአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ወደ ኒውዮርክ የተላኩት የደስታ መግለጫ ቴሌግራሞች እጅግ ብዙዎች ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ።

ሀ/ <u>ከግርማዊ ጃንሆይ፤</u>

*ይድረስ ካቶ አክሊሉ ሀብተወልድ*

*« ...... ለአገራችን ለኢትዮጵያ ይጠቅማል ብለን ከቀድሞ ጀምሮ ስንደክምበት የነበረውን የኤርትራን ጉዳይ፣ ፈጣሪያችን በዘመናችን እንዲፈጸም ስለፈቀደ፣ ደስታችንን የምንገልጸው ይህን ቸርነት ላደረገልን እግዚአብሔር ምሥጋና ማቅረብ ነው። .......*

*አንተም ለዚህ ድካማችን ተካፋይ ሆነህ፣ ትዕዛዞቻችንን በመከተል ያደረግከውን ድካም፣ በተለይም በተባበሩት መንግሥታት ለጉዳዩ ሙሉ ኃላፊነት ሰጥተንህ፣ ለመልዕክተኞቻችን መሪ ሆነህ፣ ብዙ ጊዜ ተጉዘህ፣ የፈጸምከውን አንዘነጋውም። ...... ወደ አዲስ አበባ በቶሎ እንድትመጣ ያሰብነውም በደስታው በሙሉ እኛው አጠገብ እንድትሆን ስለነበረ፣ መታመ*
*ምህን ሰንሰማ እጅግ አዘንናል። አሁንም ከጤናህ የሚበልጥ ነገር ስለሌለ፣ የሚያስፈልገውን ሕክምና ሁሉ አድርገህ እንድትመለስ እንወዳለን ....... »*

ለ/ <u>ከግርማዊት እቴጌ መነን፤</u>

*ይድረስ ካቶ አክሊሉ፤*

*« ...... ጤና ማጣትህን ሰስማ በጣም አድርጌ አዘንኩ። እኛ ሀሳባችን እዚህ መጥተህ ደስታውን አንድ ላይ እንድንካፈል ነበር። ድካምህን ሳይቆጥርልህ እንደዚህ በመታመምህ የሚያሳዝን ነው። አሁንም እግዚአብሔር መሐሪ ነውና በቸርነቱ ምሮህ በደህና ለመገናኘት ያብቃን።...... »*

*ፊርማ እቴጌ መነን*

ሐ/ <u>ከጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ፤</u>

*« ...... አንዳንድ ጊዜ እውነተኛ ደስታን በሚበቃ ቃላት መግለጥ ያስቸግራል። ለብዙ ዓመታት የደከምክበት ጉዳይ ፍሬውን ስለሰጠ፣ ከአንተ የበለጠ የተደሰትነው እኛ ነን። ይህችን ፍርድ ያገኘህባትን ቀን፣ ላንተ የሠላምና የደስታ ዘመን መክፈቻ አድርገህ ልትደሰትባት ይገባል። ይህን የምለው፣ ለአገራችን ለኢትዮጵያ ስትደክም፣ ያሳለፍከው ጭንቅና ፈተና ትዝ እያለኝ ነው። ከዚህ ቀደም ደጋግሜ ነግሬሃለሁ። እንደ አንተ ያለ ጥሩ (AVOCAT) ጠበቃ ተሟግቶ ፍርድ በማግኘቱ ብቻ ሥራው ተፈጸመለት ማለት አይደለም። እኛም ዘንድ ባለው አስተያየት የተፈረደውን ማስፈጸምም የጠበቃው ኃላፊነት ነው። ስለዚህ የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር የኤርትራን አስተዳደር ለማዘጋጀት ከመምጣቱ በፊት፤ እዚህ በሰፊው የሚጠብቅህን ሥራ አውቀህ፤ ከመመለስህ በፊት ደህና አድርገህ ታከም። የተቻለውንም ያህል ዕረፍት አድርግ። የልብ ደስታዬን የምገልጥልህ ሳገኝህ ነው። ከሙሉ ጤና ጋር እንዳይህ በፀሎት አስብሃለሁ ...... »*

መ/ <u>ካቶ ይልማ ዴሬሣ፤</u> (የንግድና የእንዱስትሪ ሚኒስትር)

BRAVO - AKLILU (ብራቮ አክሊሉ)

« ...... በኤርትራ ጉዳይ የተጣለብህን ሚሲዮን በሚያኮራ መንገድ ደከመህ ፈጸምከ:: የሞቀ ደስታዬንና ስለ ጤናህም መልካም ምኞቴን የምልክልህ፣ ከተለየ የወንድምነት ስሜት ጋር ነው:: ስለ አንተ ያልተደሰተ የለም:: ሁሉም አድንቆሃል:: አበዛው ባትለኝ፣ ያ ሙግት ገጥመህ የረታኸው ወዳጅህ ካርሎ ስፎርሳም፣ የደስታ መግለጫ ቢልክልህ የተገባ ነው
እላለሁ ......»

ሠ/ <u>ከደጃዝማች መኰንን ደስታ፤</u> (የወለጋ ጠቅላይ ገዥ)

ለወንድሜ ወዳጄ አቶ አክሊሉ፤

« ....... የኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ መቀላቀልና ለኢትዮጵያም የባሕር በር ባለቤትነቷ መመለሱ፣ የድካምህ ፍሬ ነው:: የሠራኸው ሁሉ ለአገርህና ለንጉሠ ነገሥትህ፣ ለኛም ለኢትዮጵያውያን ወገኖችህ የሚያስደስት ብቻ ሳይሆን የሚያኮራም ነው:: የተሟላ ጤና ይዘህ በሠላም ተመለስልን ...... »

ረ/ <u>ከአቶ ተድላ ባይሩ፤</u> (ያገር ፍቅር አንድነት ዋና ጸሐፊ)

ለክቡር አቶ አክሊሉ፤

« ....... በግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ታላቅ መሪነት፣ ለኛ ለኤርትራውያን ኢትዮጵያዊነታችንን ለማስገኘት፣ በኒውዮርክ ላይ የነበረዎት የሥራ ድካምና እንደዚሁም ከጠላቶቻችን ጋር የነበረዎትን ሁሉ በዓይኔ አይቼ ስለአዘንኩልዎ፣ አሁን በተገኘው ፍርድ ሠላም ያገኛሉ ብዬ በብዙ ተስፋ አድርጌያለሁ:: እዚህ ኤርትራ፣ ለኛም ለኤርትራውያኖች የደረሰን ደስታ በጣም ብዙ ስለሆነ፣ በደህና ሲመለሱ ያዩታል:: የተባበሩት መንግሥታትም ወደፊት ለኛ የሚሠራው ብዙ ነገር አለ ስለተባለ፣ እኛም ለመዘጋጀትና ለመሥራት የርስዎ መምጣት በደስታ ያስፈልገናል:: የአንድነት ያገር ፍቅር መሪዎቻችን፣ ክቡር ራስ ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤልን... ክቡር ደጃዝማች በየነ ባራኪ፣ ክቡር ጋሻ ሳላህ አህመድ ኪኪያ እና ኪዳነማርያም፣ ክቡር ደጃዝማች በየነ ባራኪ፣ ክቡር ጋሻ ሳላህ አህመድ ኪኪያ እና ሌሎቹም፣ ደስታቸውና ሰላምታቸው እንድነግርላቸው ጠይቀውኛል:: ...... »

# ለኤርትራ ሕገ መንግሥት ዝግጅት
# ኮሚሽነር ተመረጠ

ታህሣሥ 14 ቀን 1950 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ባካሄደው በአምስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ ከአባል አገሮች መካከል የቦሊቪያ መልዕክተኞች መሪ ኤድዋርዶ አንሴ ማቲየንሶ፤ (EDOARDO ANZE MATIENZO) በድምፅ ብልጫ የኤርትራ ኮሚሽነር ተብሎ፣ የፌዴሬሽኑን ሕገ መንግሥት እንዲያዘጋጅ ተመረጠ:: ከቀረቡት እጩዎች መካከል የበርማው ወኪል ቢመረጥ ለኢትዮጵያ የተሻለ እንደሚሆን ተገምቶ ነበር:: እንደሚታወሰው የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን አባል የነበረውን የበርማ መልዕክተኛ፣ ጣልያኖች በገንዘብ

ለመደለል ቢሞክሩትም፣ የኤርትራ ሕይወት ያለ ኢትዮጵያ ብቻውን ሊዘልቅ አለመቻሉን ተገንዝበ፣ የሮማን መንግሥት ሀሳብ አልተከተለም:: ከዚህም በላይ፣ የኤርትራ መፍትሔ በፌዴሬሽን እንዲሆን፣ የደቡብ አፍሪካን መልዕክተኛ ያግባባው ይኸው የበርማ ወኪል ነበር::

ከላቲን አሜሪካ አገሮች ውስጥ አንዱ የሆነው ቦሊቪያ፣ የኤርትራ ጉዳይ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ሙሉ የጣልያን ደጋፊ ስለነበረ፣ አሁንም በሕገ መንግሥቱ ዝግጅት ላይ፣ የጣልያኖችን ምኞት በመከተል ያስቸግረን ይሆናል በማለት፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከፍ ያለ ሥጋት አደረባቸው:: ተመራጩ አንሴ ማቲየንሶና አክሊሉ ሀብተወልድ የሚተዋወቁት፣ ከሀያ ዓመታት በፊት ከ1930 ዓ.ም ጀምሮ በፓሪስ የፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት በሚያጠኑበት ጊዜ ነበር:: ሆኖም፣ የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ምክር ቤት የኤርትራን ዶሴ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ካዛወረ በኋላ፣ አንሴ ማቲየንሶ የአገሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበረበት ጊዜ እና ኋላም የመልዕክተኞች መሪ እየሆነ ኒውዮርክ ሲመጣ፣ ለጣልያን መንግሥት ደጋፊነቱን በግልጽ ሲያሳይ የቆየ ስለሆነ፣ ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ጋር በወዳጅነት መቀራረብ አልቻሉም:: በመጨረሻው፣ በታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም ጠቅላላው ጉባኤ የኤርትራን ጉዳይ ሲወስን፣ የቦሊቪያ መልዕክተኛ በአገሩ ስም ሆኖ የድጋፍ ድምፁን ቢሰጥም፣ አቶ አክሊሉ በወጣትነት ዘመን በተማሪ ቤት የሚያውቁት ወዳጃቸው ጣልያናዊ ስሜቱን ለውጧል ብለው አላመኑትም:: ስለዚህ፣ ለኤርትራ ሕገ መንግሥት አዘጋጅነት የተሾመው ሰው ከጣልያን ደጋፊዎች መካከል አንዱ ስለሆነ፣ ለኢትዮጵያ ምቹ እንደማይሆን በመገመት ብርቱ ጥንቃቄ እንዲደረግ ተሞከረ:: በመጀመሪያ መደረግ ያለበት ኮሚሽነር አንሴ ማቲየንሶ አሥመራ ደርሶ በተባበሩት መንግሥታት ለንደቅ ዓላማ ጽሕፈት ቤቱን ከማቋቋሙ በፊት፣ አዲስ የንጉሡ ነገሥቱ ላይዘን ኦፊሰር መሾም ነው ተባለ::

## በአሥመራ አዲስ ላይዘን ኦፊሰር

« ...... በኤርትራ ጉዳይ እስካሁን ድረስ፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተደረገው ትግልና የተፈጸመው ሞያ፣ እስከምን እንደነበረ ለመመራመርና፣ ለታሪክ ለማቅረብ ወደፊት በቂ ጊዜ ስለሚኖረን፣ አሁን የመጀመሪያው ምዕራፍ እንደተዘጋ ቆጥረን፣ አዲስ የሚጀመረው የሁለተኛው ምዕራፍ፣ እጅግ የሚያሳስበን መሆኑን መረዳት አለብን ...... » በማል መግቢያ፣ አቶ አስፍሐ ወልደሚካኤል ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ባቀረቡት ማስታወሻ፣ በኮሎኔል ነጋ ቦታ አዲስ ላይዘን ኦፊሰር እንዲሾም አሳሰቡ:: በመሠረቱ፣ የኮሎኔል ነጋ ኃይለሥላሴን መዛወር አስፈላጊነት፣ ካቶ አስፍሐ ቀደም ብለው በዚያን ጊዜ የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር የነበሩት አቶ ዘውዴ ገብረሕይወት (ኋላ ቢትወደድ) ከጃንሆይና ከጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ ጋር ተነጋግረውበት ነበር:: አዲስ ላይዘን ኦፊሰር እንዲሾም አስፈላጊነቱን አቶ ዘውዴ ገብረሕይወትና አቶ አስፍሐ አስተያየታቸው ተመሳሳይ የሆነው፣ ሁለቱም ሰዎች በኮሎኔል ነጋ ላይ ቂም ኖሮዋቸው ወይም እስካሁን የተሠራው ሥራ ሁሉ የሚነቀፍ ነው በማለት አይደለም::

ነጋ ኃይለሥላሴ ለአምስት ዓመታት ያህል፣ የንጉሠ ነገሥቱ ላይዘን ኦፊሰር ሆነው ኤርትራ በቆዩበት ጊዜ፣ የአንድነቶች ትግል ዋና መሪ ናቸው በመባል፣




ለኤርትራ ሕገ መንግሥት አዘጋጅነት የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ሆኖ የተመረጠው፡ ኤድዋርዶ አንሴ ማቲየንሶ የቦሊቪያ መልዕክተኞች መሪ፤

(ኒውዮርክ ታህሣሥ 1950 ዓ.ም)
(ፎቶ U.N)

የተቃዋሚዎቹ ወገኖችና ጣልያኖቹ፣ በጠላት መልክ ሲመለከቷቸው ኖረዋል። ኮሎኔል ነጋም ለዚህ ሳይበገሩ፣ የሚደረግባቸውን ቁጭና የሚጠመድባቸውን አደጋ ፊት ለፊት መክተው ሚሲዮናቸውን በትክክል ፈጽመዋል። አሁን የዚያ አጅግ አስቸጋሪ የነበረው የትግል ዘመን ተዘግቶ፣ አዲሱ የዲፕሎማሲ ሥራ ሲጀመር፣ ከተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ጋር በቅርብ ሆኖ በሕገ መንግሥቱ ዝግጅት ላይ የሚካፈል አዲስ ላይዘን ኦፊሰር መሾም፣ አስፈላጊነቱን የተስማሙበት ብዙዎች ናቸው። ኮሎኔል ነጋም የኤርትራ ጉዳይ በፌዴሬሽን መልክ የተወሰነው ከሕዝቡ ፍላጐትና ስሜት ውጭ ነው በማለት እጅግ ቅር የተሰኙ ስለሆኑ፣ ከተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነሮ ጋር ባላመኑበት የፌዴሬሽን አስተዳደር ዝግጅት ላይ መተባበር ያዳግታቸዋል ተብሎ ተገምቷል።

አቶ አስፍሐ ወልደሚካኤል ለጃንሆይ በጻፉት ደብዳቤ፣ በኮሎኔል ነጋ ኃይለሥላሴ ቦታ የሚሾመው ላይዘን ኦፊሰር፣ በኤርትራ ውስጥ ባሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘንድ፣ ከዚህ በፊት ቀጥታ ግንኙነት ያልነበረው አዲስ ሰው እንዲሆን አመልክተዋል። ከዚህም ጋር አያይዘው አዲሱ ተሿሚ ምንም እንኳን በሕዝቡ ዘንድ እንግዳ መስሎ እንዲታይ ቢያስፈልግም፣ የኤርትራን ጉዳይ በቅርብ የተከታተለ፣ በተባበሩት መንግሥታት ባለሥልጣኖችና በእንግሊዞቹ ዘንድ ተደማጭነት የሚኖረው ሰው እንዲሆን አሳስበዋል። የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር ዘውዴ ገብረሕይወትም፣ አዲሱ ላይዘን ኦፊሰር የጋዜጣና ማስታወቂያ ዋና ዲሬክተር አቶ አምደሚካኤል ደሣለኝ እንዲሆኑ እጩ አድርገው አቀረቧቸው። የአምደሚካኤል ሹመት በይፋ ከመገለጹ በፊት፣ በዚያን ጊዜ ለሕክምና አውሮፓ የሚገኙት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ አስተያየታቸውን እንዲስጡ በቴሌግራም ተጠየቁ። ከገነተ ልዑል ቤተመንግሥት የተላከላቸውም መልዕክት፤

« ...... የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር አሥመራ መጥቶ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት፣ በነጋ ኃይለሥላሴ ቦታ አዲሱ ላይዘን ኦፊሰር አምደሚካኤል ደሣለኝ እንዲሆን ስለቀረበልን፣ ያንተን ሀሳብ በቶሎ ግለጥልን ....... » የሚል ነበር። አቶ አክሊሉ አዲስ ስለሚሾመው ላይዘን ኦፊሰር የተለየ አስተያየት አቀረቡ።

« ...... ግርማዊነትዎ እንደሚያውቀው ከእንግዲህ ወዲህ አሥመራ ላይ የሚገጥመን ትልቁ ሥራ የሕግና የዲፕሎማሲ ጉዳይ ነው። የወደፊቱ የላይዘን ኦፊሰር ሚሲዮን፤ ካለፈው ኃላፊነትና የሥራ ዓይነት ጋር የተለያየ ስለሆነ፤ በኮሎኔል ነጋ ቦታ ሌላ ሲቪል ሰው መታሰቡ ጥሩ ነው። ሆኖም ኮሎኔል ነጋ የሚዛወረው እስከዛሬ የፈጸመው አገልግሎት ሁሉ በጣም ጥሩ ሥራ መሆኑ ታውቆለትና ተመስግኖ እንዲሆን፤ የበኩሌን አስተያየት በትህትና አቀርባለሁ። አዲስ ስለሚሾመው ላይዘን ኦፊሰር ጃንሆይ ቢፈቅዱልኝ፣ የኔ ምርጫ አቶ ገብረመስቀል ክፍለእግዚአ ዋና ሆኖ፣ አቶ አምደሚካኤል ደሣለኝ ምክትል ቢሆን ነው። ገብረመስቀል፣ በተባበሩት መንግሥታት ከእኛው ጋር በቅርብ የሠራ እና የኤርትራን ጉዳይ አወሳሰን በዝርዝር ስለሚያውቀው፣ የዩናይትድ ኔሽን ኮሚሽነር ሊያከብረውም ሊያደምጠውም ይችላል። አምደሚካኤልም በፕሮፓጋንዳ ሥራ ደህና ልምድ ያለውና የጣልያኖቹንም ተንኮል መከታተል ስለሚያውቅበት፣ የሁለቱ ሰዎች የችሎታ ትብብር ደህና ውጤት ሊሰጥ ይችላል የሚል እምነት አለኝ ..... »

ስለ ገብረመስቀል ክፍለእግዚአ፤ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስም መልካም አስተያየት ስላላቸው፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የቀረበውን ሀሳብ ደግፈው፣ ሹመቱ

እንዲታወጅ የጃንሆይም መልካም ፈቃድ ተገኝቶ ነበር። ነገር ግን፡ ልጁ የኤርትራ ተወላጅ በመሆኑ አንዳንድ ተንኮለኞች አደጋ ሊጥሉበት ይችላሉ ብለው፣ አባታቸው ብላታ ክፍለእግዚአ ይሕደጎ ስለተጨነቁና ስለአመለከቱ፣ የገብረመስቀል ሹመት ሳይፈጸም ቀረ። ወዲያው፡ ብላታ ኪዳነማርያም አበራ (የጃንሆይ ባለሟል) በጻፉት ልዩ ማስታወሻ፣ ለሳይዘን አፊሰርነቱ ቦታ 1ኛ/ ኮሎኔል ኢያሱ መንገሻ፣ 2ኛ/ አቶ ሥረቀ ብርሃን ገብረ እግዚአ እጩዎች እንዲሆኑ ሀሳብ ስለአቀረቡ፡ የጽሕፈት ሚኒስትሩ አስተያየት እንዲሰጡበት ንጉሠ ነገሥቱ አዘዙ። ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስም ስለእነዚህ ሁለት እጩዎች የሚከተለውን ትችት ሰጡ።

1. ኮሎኔልን በኮሎኔል መተካት ያስፈልጋል ካልተባለ በስተቀር፣በአሥመራ የሳይዘን አፊሰርነት ሥራ ለኢያሱ ተስማሚ ነው ብዬ አላምንም። ኢያሱም ቢጠየቅ፣ ሥራው ይስማማኛል እንደማይል የታወቀ ነው።

2. አቶ ሥረቀ ብርሃን ገብረእግዚአ፣ ኢትዮጵያዊነቱና አገር መውደዱ እንከን የማይገኝለት ነው። ነገር ግን እጅግ ቁጡ እና ፈጥኖ ፈራጅ በሆነው ጠባዩ፣ ለዚህ ብዙ ትዕግሥት ለሚጠይቅ ሥራ ጥሩ ምርጫ አይሆንም።

...... በዚህ ሁሉ ምክንያት አሁን ጊዜ እንዳይጠፉብን፣ አቶ ዘውዴ ገብረሕይወት የበላይ ሆኖ በቅርብ እየተቆጣጠረው፣ አምደሚካኤል ደሣለኝ ሳይዘን አፊሰር ቢሆን ይሻላል ሲሉ፣ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ ያቀረቡትን ሀሳብ ጃንሆይ አጽድቀው ሹመቱ ተፈጸመ።

የአንድነት ወገኖች የኮሎኔል ነጋ ኃይለሥላሴ መዛወርና የአቶ ዓምደሚካኤል ደሣለኝ መተካት ምክንያቱ ለምን እንደሆነ በዝርዝር የሚያውቁት አልነበራቸውም። የተባበሩት መንግሥታት የሰጠው ፍርድ በሥራ እስኪገለጥ ድረስ ብዙ ድካም አለባችሁ ከተባልን፣ ከለመድናቸው ከነጋ ኃይለሥላሴ ጋር መቀጠሉ አይሻልም ኖርዋል ወይ ? የሚሉም አልጠፉም። ሆኖም አርበኛው ኮሎኔሉን በወግ ሸኝተው፣ የጣልያኖችን ተንኮል በማወቅ ባለሞያ ናቸው የተባሉትን ዓምደሚካኤልን በወግ ተቀብለዋል።

## የማቲየንሶ ሕገ መንግሥት

የኤርትራን መተዳደሪያ እንዲያዘጋጅ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የተሾመው፣ የቦሊቪያ ተወላጅ አንሴ ማቲየንሶ (ANZE MATIENZO) የተሰጠው ሥልጣን እጅግ ከፍ ያለ መሆኑ ተስምቶታል። በተለይም አንድ የላቲን አሜሪካ አገር ተወላጅ ከኢንተርናሽናል ሸንጎ ይህን የመሰለ ኃላፊነት ሲቀበል ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ፣ ውጤቱ ያማረና መልካም ዝና የሚኖረው እንዲሆን ከልቡ ተመኝቷል። ሆኖም የሚያስበውና የሚመኘው ሁሉ በጥሩ ሁኔታ ሊሳካለት የሚችለው፣ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት እና ኤርትራን ከሚያስተዳድሩት ከታላቋ ብሪታንያ ባለሥልጣኖች ጋር፣ እንደሚኖረው መልካም ትብብር መሆኑን፣ ማቲየንሶ በመጀመሪያው ደረጃ አልተረዳም ነበር። ሥራውን ለመቀጠል አሥመራ ከመድረሱ በፊት፣ በሚያዘጋጀው የሕገ መንግሥት ረቂቅ ለፌዴራሉ መንግሥት ለኢትዮጵያና፣ ለፌዴሬሽኑ አስተዳደር ስለሚከፋፈለው

የሥልጣን ድርሻ፣ ከጣልያኖችና ከአንዳንድ ተንኮለኞች ልዩ ልዩ ምክር ሲቀርብለት እንደሰነበተ አንዳንድ መረጃዎች አመልክተዋል።

ጣልያኖች የሚጥሩት፣ ማቲየንሶን በእጅ አዙር ይዘው፣ በሕገ መንግሥቱ ዝግጅት ላይ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን በተቻለ መጠን እንዲዳከምና፣ የአቶኖሚው አስተዳደር በአገር ውስጥም ብቻ ሳይሆን በውጭ ጉዳይ እና በውጭ ንግድ በኩል፣ የሥልጣን ድርሻ እንዲኖረው ለማስደረግ ነው። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደግሞ በበኩላቸው ከኮሚሽነሩ የሚጠብቁት፣ በታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት የሰጠውን የፌዴራል አክት ውሳኔ ተመርኩዞ፣ ከኢትዮጵያም ጋር በቅርብ እየተመካከረ፣ የሕገ መንግሥቱን ዝግጅት እንዲያጠናቅቅ ነው። ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ችላ ብሎ፣ ማቲየንሶ በግል አስተያየቱና የጠላት አገሮች በሚሰጡት ምክር የሚመራ ሆኖ ከተገኘ፣ ኢትዮጵያ የራሷን አቋም በፍጥነት መውሰድ እንደሚገባት፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ንጉሠ ነገሥቱ በቅድሚያ እንዲያውቁትና እንዲዘጋጁበት አድርገዋል።

የማቲየንሶ አስተያየት፣ ኤርትራ በንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ሥር በፌዴራሲዮን መቀላቀሏና፣ ፌዴራል የሆነውም የኢትዮጵያ መንግሥት የመላውን የኤርትራን ግዛት ደህንነት ለመጠበቅና፣ የባሕር በሮቹንም በቀጥታ ለማስተዳደር በቂ ሥልጣን ስለተሰጠው፤ የአቶኖሚው መንግሥት በውስጥ አስተዳደሩ ሰፋ ያለ

መብት ቢኖረው፣ ኢትዮጵያን ቅር የሚያሰኝ ነገር አይታየኝም የሚል ነው። ይህን አስተያየት ውጭ ውጭውን እየነዛ፤ ውስጥ ውስጡን ግን ጣልያኖቹንና የአንድነት ተቃዋሚዎቹን ለማስደሰት አንዳንድ ተንኮል ሲያዘጋጅ ሰንብቷል።

የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር አሥመራ ደርሶ የተዘጋጀለትን ቢሮ ከተረከበ በኋላ፤ የመጀመሪያ ሥራው አዲስ አበባ መጥቶ፣ ንጉሠ ነገሥቱንና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ማነጋገር ነበር። የካቲት 19 ቀን 1950 ዓ.ም፣ በኢትዮጵያ ዋና ከተማ መልካም አቀባበል ከተደረገለት በኋላ፣ በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ከንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን ቀርቦ ካደረገው ንግግር ፍሬ ነገሮቹ የሚከተሉት ናቸው።

« ...... በግርማዊነትዎ ዘውድ ሥር ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትተዳደር የተባበሩት መንግሥታት ያደረጉት ውሳኔ፣ የሕዝቦቹን ምኞት የሚያሟላና አዲስ የሕይወት ብርሃን የሚሰጥ ነው። ....... በታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም የተደረጉት እነዚህ ውሳኔዎች፣ በትክክል እንደሚከበሩና በተግባር ላይ እንደሚገለጡ፣ የተባበሩት መንግሥታት በግርማዊነትዎ ላይ ከፍ ያለ ዕምነት ጥለዋል። ...... እኔም የተባበሩት መንግሥታት የጣሉብኝን ከፍተኛ አደራ የተቀበልኩት፣ በታላቅ ክብርና ስሜት ስለሆነ፣ በማናቸውም አኳኋን የተሰጠኝን ኃላፊነት በትክክል ለመፈጸም የተዘጋጀሁ መሆኔን፣ ለግርማዊነትዎ ማረጋገጥ እወዳለሁ። ...... ይህንንም ከፍተኛ አደራ በተግባር ላይ ማዋል የሚቻለው፣ ከግርማዊነትዎ መንግሥት በማገኘው ሙሉ እርዳታና ሕብረት ነው። ....... »

ከዚህ በላይ የተገለጸው የማቲየንሶ አነጋገር በትክክል የሚያሳየው፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያን የሚገዟት፣ በፊውዳል ሥርዓት ስለሆነ፣ ዴሞክራቲክ የሆነውን የፌዴሬሽን አስተዳደር አይቀበሉም በማለት፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች ደህና አድርገው በፕሮፓጋንዳ ያደነቆሩት መሆኑን ነው። በዚህ ምክንያት፣



ኮሎኔል ነጋ ኃይለሥላሴ (ኋላ ሌፍትናንት ጄኔራል)
በአሥመራ የንጉሠ ነገሥቱ ላይዘን ኦፊሰር፣

(1946 - 1950)

የተባበሩት መንግሥታት ለኤርትራ ሕገ መንግሥት ዝግጅትና ለአፈጻጸሙ፣ በግርማዊነትዎ ላይ ከፍ ያለ ዕምነት ጥለዋል እያለ፣ በሪፖርቱ ውስጥ ይህችን « ዕምነት » የምትባል ቃል ደጋግሞ እያጠነከረ ተናግሯል። ኮሚሽነሩ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ፣ የጠላት ወገኖች በሚያምታቱት ሀሳብ አእምሮው የተጨናነቀ መሆኑ ቀደም ብሎ ታውቆ ስለነበረ፤ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሰጡት መልስ፣ በትክክሉ የሚያስቡትን አልሸሸጉም። የተባበሩት መንግሥታት ይህን ውሳኔ የሰጠው፣ የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎቱ ምን መሆኑ መታወቅ አለበት ተብሎ፣ ሁለት ጊዜ መርማሪ ኮሚሽን ከተላከ በኋላ፣ ጉዳዩ በየጉባኤው ብዙ ክርክር ሲደረግበትና ከአንዱ ስብሰባ ወደ ሌላው በቀጠሮ እየተላለፈ፣ ረጅም ጊዜ ፈጅቶ መሆኑን፣ ኮሚሽነሩ ትልቅ ትኩረት እንዲሰጠው፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሰፊው አስገንዝበዋል። ከዚህም እያይዘው፣ ኢትዮጵያ በአምስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተደረገውን ውሳኔ እንድትቀበል፤ ለመልዕክተኛቸው ሥልጣን የሰጡት፣ የተባበሩት መንግሥታት ኃላፊነቱን ለመፈጸም፤ ከዚህ ሌላ ማድረግ የማይችል መሆኑን በመረዳት ነው ካሉ በኋላ፤ ይህ የፌዴሬሽን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ባያስደስታቸውም፤ ለኮሌክቲፍ ሴኩሪቲ ባላቸው መሠረታዊ አቋም፣ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ እንደሚከበር ለኮሚሽነሩ አረጋገጡለት። ንጉሠ ነገሥቱ፣ ለኤርትራ አስተዳደር የተደረገውን ውሳኔ በሥራ ለማስፈጸም፣ በመንግሥታቸው በኩል የተቆረጠ መሆኑን ካስታወቁ በኋላ፣ እንደዚሁም <u>በተባበሩት መንግሥታት ባለሥልጣኖች በኩል፤ መተማመን፣ መተባበርና እውነተኛውን የአገሩን ሕዝብ ጉዳይ በጥልቅ በመረዳት፣ ጥረት እንዲደረግ ጠይቀዋል።</u>

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው፣ ጃንሆይ ስለሰውየው ደህና መረጃ ደርሷቸው ስለነበረ፣ ትክክለኛ ዕምነታቸውንና አስተያየታቸውን ነግረውታል። ኮሚሽነሩ አዲስ አበባ በቆየበት ሰሞን፣ በተለይ ከንጉሠ ነገሥቱና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጋር በሰፊው ሲነጋገር፤

1ኛ/ የሚዘጋጀው ሕገ መንግሥት፣ ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም በቁጥር 390 V የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው ውሳኔ መሠረት ብቻ መሆን እንዳለበት፤

2ኛ/ የፌዴሬሽኑ ውሳኔ ትክክለኛ ትርጉሙ፣ ለኤርትራውያኖች የውስጥ አስተዳደር መብት እንዲሰጣቸው ነው እንጂ፤ በሁለት በተለያዩ አገሮች መካከል እንደሚደረግ የፌዴሬሽን ግንኙነት፣ የኢንተርናሽናል ታዋቂነት የሌላቸው መሆኑ በትክክል እንዲረጋገጥ፤

የኢትዮጵያ መሠረታዊ ዕምነት መሆኑን እንዲገነዘበው፤ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ተሰጥቶታል። ይሁን እንጂ ኮሚሽነር ማቲየንሶ የኢትዮጵያን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ማዳመጥ አልፈለገም። በተለይ ከጣልያን መንግሥትና ከአንዳንድ የላቲን አሜሪካ ወገኖቹ የሚደረግበት ተፅዕኖ ብዙ ስለሆነ፤ እየደጋገመ የሚናገረው፣ የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች የሚፈለቀቁት፣ በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ መሠረት ቢሆንም፣ የኤርትራ የውስጥ መንግሥት ለአገሩ ዕድገትና ልማት እንዲጠቅመው፣ ሰፋ ያለ ሥልጣን ሊኖረው ይገባል እያለ ነው። <u>ምን ዓይነት ሥልጣን ?</u>

የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ፣ ለፌዴራሉ መንግሥት መሪ ለንጉሠ ነገሥቱ ከተዘረዘሩት የኃላፊነት ድርሻዎች ውጭ የሆኑትን ጠቅላላ ጉዳዮች፣ የኤርትራ የውስጥ መንግሥት በሙሉ ሥልጣን እንደሚያከናውን ግልጽ አድርጉ

አቅርቦለታል:: ይህንን መሠረት አድርጐ ሕገ መንግሥቱን በመተንተን ፋንታ፣ የአቶኖሚውን ሥልጣን ማስፋፋትና ማጠንከር ያስፈልጋል የሚባለው ደረቅ ሀሳብ ትርጉም የለውም ተብሎ፣ ከኢትዮጵያ በኩል አቋም ተወስዷል:: የጣልያን መንግሥት ደግሞ በበኩሉ ማቲየንሶን ወጥሮ የያዘው፣ በተቻለ መጠን የሚዘጋጀው ሕገ መንግሥት፣ የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን ሸፈንፈን አድርጐ፣ የኦቶኖሚውን ሥልጣን የሚያጐላ እንዲሆን ነው:: ይኸውም፣ ኤርትራውያኖች በኢንተርናሽናል ግንኙነት በኩል የሥልጣን በር ሳይዘጋባቸው፣ ለአገራቸው ልማትና ዕድገት የውጭ እርዳታ ለማግኘትና፣ ለኢኮኖሚያቸውም የውጭ ንግዳቸውን ለማዳበር የሚያስችላቸውን ዕድል እንዲያገኙ ነው:: ማቲየንሶ፣ በዚህ ሀሳብ ተመርቶ ሕገ መንግሥቱን ካዘጋጀ በኋላ፣ ኢትዮጵያ አልቀበልም ብላ ጉዳዩ ለዩናይትድ ኔሽን የቀረበ እንደሆነ፣ ለኤርትራ መፍትሔው ነፃነት ነው ተብሎ ይወሰናል፣ የሚል ተስፋ ጣልያኖች አሳድረዋል::

ኮሚሽነሩ፣ ከኢትዮጵያ የተሰጠውን አስተያየት በጥሞና እንዳላዳመጠው ሁሉ፣ ከአሜሪካና ከጣልያንም የቀረበለትን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል አልተመቸውም:: ከአሜሪካና ከእንግሊዝ፣ ከፈረንሣይና ከስዊስ አገሮች አራት የሕግ አዋቂዎች በብዙ ገንዘብ ቀጥሮ፣ ዜኔቭ ላይ የሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ከመዘጋጀቱ በፊት፣ በአሥመራ ቢሮው የኤርትራን ሕዝብ እየተቀበለኩ፣ አስተያየቱን በቀጥታ ማዳመጥ አለብኝ ብሎ የጀመረው ፕሮግራም ውጤት ሳያገኝ ቀረ:: ሕዝቡ ለሰቡተኛ ጊዜ ለወደፊት ዕድሉ ሀሳቡን እንዲገልጽ መርማሪ ኮሚሽን የተላከበት ስለመሰለው፣ የኮሚሽነሩን ቢሮ አጥለቅልቆ ሲይዘውና ብዙ ትርምስ ሲፈጠር፣ ያቀደውን ፕሮግራም ወዲያውኑ መሰረዝ ግዴታ ሆነበት:: ማቲየንሶ፣ የሕዝቡን አስተያየት ማዳመጥ አለብኝ ያልኩት፣ ለሕገ መንግሥቱ ዝግጅት የተባበሩት መንግሥታት ከወሰናቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ውጭ፣ ባልተብራሩት አንዳንድ ነጥቦች ላይ ነው ብሏል:: እነዚህንም መብራራት ያስፈልጋቸዋል የሚላቸውን ጥያቄዎች ያቀረበው፣ በሚከተለው መልክ ነበር::

1. ለኤርትራ <u>ሁለት ምክር</u> ቤት፣ የሕግ መምሪያና የሕግ መወሰኛ ያስፈልጋል ወይ ?

2. የሕዝብ ምክር ቤት አባሎች የሚመረጡት፣በቀጥታ በሕዝቡ ነው? ወይስ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ በሕዝብ ዋና ዋና ተወካዮች ?

3. የኤርትራ መንግሥት መሪ ሥልጣን የሚቀበለው በሹመት ነው? ወይስ በፓርላማ ምርጫ ?

4. የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በኤርትራ መሪ አሿሿም ወይም አመራረጥ ላይ ምን ዓይነት ሚና ሊኖራቸው ይገባል ?

5. የኤርትራ ሕዝብ አፊሲየል ቋንቋዎች የሚሆኑት የትኞቹ ናቸው?

6. ለኤርትራ የተለየ ባንዲራ ያስፈልጋታል ወይ ?

ማቲየንሶ፣ የሕዝቡን አስተያየት ማወቅ አለብኝ ያለው፣ በእነዚህ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ከሆነ፣ በቀጥታ ከሕዝቡ ጋር መነጋገርና ተደማምጦ መልሱን ማግኘት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን መገመት ነበረበት:: እንኳንስ በኤርትራ ቀርቶ፣ በሥልጣኔ እጅግ በገፉትም አገሮች ዘንድ፣ እነዚህን በመሳሰሉት ጥያቄዎች ላይ

ሀሳብ መለዋወጥ የሚቻለው ከሕዝብ ተመራጮች ጋር ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው:: ማቲየንስ ከሕዝቡ ጋር ቀጥታ ለመወያየት ያጋጠመውን ችግር ከተረዳ በኋላ፣ በኤርትራ ካሉት ልዩ ልዩ የፖለቲካና የሀይማኖት መሪዎች፣ እንደዚሁም በየገጠሩ ካሉት ያገር ሽማግሌዎች ጋር በመነጋገር አንዳንድ አስተያየት መቃረም ይቻላል ብሎ ሞከረ::

እንደሚታወቀው፤ በኤርትራ ውስጥ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ለመሆን ሲታገል የኖረው ሕዝብ፣ እንኳንስ ስለ መንግሥት መሪ ምርጫ እና ስለ አዲስ ባንዲራ ጉዳይ ለመወያየት ቀርቶ፤ በጠቅላላው የሕገ መንግሥት ዝግጅት የሚባለውንም ሀሳብ መስማት አይፈልግም:: በአንድነት ወገኖች አስተያየት፤ ለኤርትራ የተለየ ሕገ መንግሥት እንዲዘጋጅ የተወሰነው፣ ከእናት አገር ጋር የአስተዳደር ልዩነት በመፍጠር የሁለቱን ሕዝቦች አንድነት ለማራራቅ የታሰበ የጠላት ተንኮል ነው ተብሎ ታምኖበታል:: ከጠቅላላው ሕዝብ በጣም አነስተኛ የሆነው የተቃዋሚው ክፍል ደግሞ፣ አስተዳደሩ በምን መልክ ይሁንልሁ ? ተብሎ እንደገና የመጠየቅ ዕድል ካጋጠመው፤ አስተያየቱ ከማቲየንስ ፍላጐት እጅግ ርቆ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን በተቻለ መጠን ከኤርትራ ግዛት እንዲርቅ ይደረግልን እንደሚል የታወቀ ነው:: ሌሎቹ ሊበራል ተቃዋሚዎች የሆኑትና የጣልያን ተወላጆች፤ በእርግጥ በኮሚሽነሩ ሥልጣን ብቻ የምንፈልገውን ሁሉ እናገኛለን ብለው አያልሙም:: ሆኖም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ተስፋ የሚያደርጉት፣ እንሴ ማቲየንስና እክሊሉ ሀብተወልድ ተጣልተው ጉዳዩ ለተባበሩት መንግሥታት ሲቀርብ፣ <u>የነፃነት ደጋፊዎች ሊያሸንፉ ይችላሉ</u> ብለው ነው::

የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ለልዩ ልዩ የፖለቲካ መሪዎችና የሀይማኖት አባቶች ላቀረባቸው ጥያቄዎች፤ ከአብዛኞዎቹ ያገኛቸው መልሶች፤ እሱ እንደተመኘው ለአቶኖሚው መንግሥት ሥልጣን ማስፋፊያ ወይም ማጠንከሪያ የሚረዱት ሳይሆኑ ቀሩ:: ይህም ሊሆን የቻለው፤ ዓምደሚካኤል ደሣለኝ የንጉሠ ነገሥቱ ላይዘን ኦፊሰር፣ ባላቸው የተፈጥሮ ብልሀነትና የሕዝብ ግንኙነት የሥራ ልምድ፤ የአንድነት ወገኖችን በሙሉ አስተባብረው፣ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሚያምኑበት ተገቢውን መልስ በብዛት እንዲሰጡ በማድረጋቸው ነው:: የአንድነት ወገኖች፣ ጥያቄዎቹ ተዘርዝረው በደረሷቸው ጊዜ፣ መልስ አያስፈልግም ብለው በሩን እንደዘጉት ቀጥለውበት ቢሆን ኖሮ፤ ማቲየንስ ከጥቂቶቹ ተቃዋሚዎች በሚያገኘው አስተያየት ብቻ ተመርኩዞ፣ ሥራውን ለማከናወን ይሞክር ነበር:: በአቶ ዓምደሚካኤል መልካም ጥረት ከአንድነቶች በብዛት የተላከው መልስ የማቲየንስን የተንኮል ሩጫ እንዲያዘገም አስደረገው::

ሀ/ ለኤርትራ አስተዳደር የሚቋቋመው፤ ከሕግ መምሪያ ምክር ቤት በስተቀር፣ ኮሚሽነሩ የጠቀሱት የሕግ መወሰኛው (ሴኔት) አያስፈልግም::

ለ/ ከአሥመራ ከተማና ከምፅዋ ነዋሪዎች በስተቀር፤ የሌሎቹ አውራጃዎች ሕዝብ የፓርላማ መማክርቶችን በቀጥታ ለመምረጥ ችሎታው አይፈቅድለትም:: ስለዚህ፤ በየአውራጃውና በየወረዳው ባሉት፣ ሕዝቡ በሚያከብራቸውና በሚከተላቸው ያገር ሽማግሌዎች አማካይነት፣ መማክርቶቹ ሊመረጡ ይችላሉ::

ሐ/ የመንግሥቱ መሪ የተባለው የኤርትራ አስተዳዳሪ፣ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሾም አለበት:: አስተዳዳሪው ለፓርላማው ተጠያቂ ቢሆንም፣ በይበልጥ ኃላፊነቱ



ኤድዋርዶ አንሴ ማቲየንሶ ለኤርትራ ኮሚሽነር ሆኖ ከተመረጠ በኋላ፣ ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር፣

*« ...... የሚዘጋጀው ሕገ መንግሥት፣ ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም በቁጥር 390 V የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው ውሳኔ መሠረት መሆን አለበት ....... »*

(አክሊሉ ሀብተወልድ ታህሣሥ 1950)
(ፎቶ U.N)

ለንጉሠ ነገሥቱ ነው። አንድ ከባድ ስሕተት ደርሶ አስተዳዳሪው ከሥልጣን እንዲወርድ ባስፈለገ ጊዜ፡ ምክር ቤቱ ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርቦ ያሽረዋል።

መ/ የኤርትራውያን የሥራ ቋንቋ ትግርኛ ሆኖ፣ የፌዴራሉ መንግሥት ኦፊሴል ቋንቋ የሆነው አማርኛ መግባት አለበት። ዓረብኛ እንዲጨመር ከአንዳንድ ወገኖች የሚቀርበው ሀሳብ ሀይማኖትን ተመርኩዞ ስለሆነ፣ የአገሪቱ የሥራ ቋንቋ መሆን አይችልም።

መ/ የኢትዮጵያዊት ኤርትራ ሰንደቅ ዓላማ፣ አረንጓዴ ብጫ ቀይ የሆነው የአባቶቻችን የጥንቱ ባንዲራችን ነው። ለዚህች ባንዲራ ብዙ ኤርትራውያን ደማቸውን ያፈሰሱላትና የተሰዉባት ስለሆነ፣ አዲስ ሰንደቅ ዓላማ ቢፈጠር የኤርትራ ሕዝብ አይቀበልም።

እጅግ አብዛኛው የሆነው የኤርትራ ሕዝብ የሚከተላቸውና የሚያምናቸው፡ የፖለቲካና የሀይማኖት መሪዎች፣ በዝርዝር የሰጡት አስተያየት ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን፣ በጣም ጥቂቶች የሆኑት የተቃዋሚዎች ወገኖች ደግሞ፣ በበኩላቸው ባቀረቡት ሀሳብ፣ ከአንድነቶች የሚለዩት በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ነበር።

1. ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት በሰጠው ውሳኔ ላይ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ተዘርዝሮ የተሰጣቸው ሥልጣን በቂ ስለሆነ፣ ተጨማሪ አያስፈልግም።

2. የሚቋቋመው ፓርለማ፣ ሕግ ለማውጣት ብቻ ሳይሆን፣ የኤርትራን መንግሥት መሪ ለመምረጥና ለመሻር፣ ሥልጣን እንዲኖረው ያስፈልጋል።

3. የኤርትራ የሥራ ቋንቋዎች፣ ትግርኛና ዓረብኛ እንዲሁም ጣልያንኛ መሆን አለባቸው።

4. ለኤርትራ ከኢትዮጵያ የተለየ የፌዴሬሽን ባንዲራ ያስፈልጋታል።

የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር በዚህ አኳኋን ከኤርትራ ሕዝብ ተጠሪዎች የአብዛኛዎቹንና የአነስተኞቹን ሀሳብ ሲያዳምጥ ከከረመ በኋላ፣ ወደ ገኔቭ ሄዶ ከአሜሪካና ከእንግሊዝ፣ ከፈረንሣይና ከስዊስ፣ አውጣጥቶ ከቀጠራቸው የሕግ ባለሞያዎች ጋር፣ የኤርትራን ሕገ መንግሥት አረቀቀ።

የማቲየንሶ ሕገ መንግሥት መጀመሪያ በአሥመራ፣ ቀጥሎ በገኔቭ፡ ሲፈተግና ሲበጠር ለአንድ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ፣ ለኤርትራ ሕዝብ ተወካዮች ከመቅረቡ በፊት በረቂቁ ላይ ሰፍረው የታዩት ዋና ጉዳዮች፣ በኢትዮጵያ በኩል ጨርሶ ተቀባይነት የማይኖራቸው ሆኑ። እነዚህም፣ <u>የመጀመሪያው አንቀጽ፣</u> የፌዴሬሽኑ አስተዳደር በሥራ ላይ መዋል ከጀመረ በኋላ፣ <u>በፌዴራሉ አክት ላይ ወደፊት የሚሻሻል ነገር ቢኖር፣ ወይም ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ቢፈለግ፣ ውሳኔው የሚጸድቀው በተባበሩት መንግሥታት</u> ነው የሚለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ፣ የኤርትራ ፓርለማ የሚያወጣቸው ሕጎች ከመታወጃቸው በፊት፣ ንጉሠ ነገሥቱ የቬቶ ሥልጣን ይኖራቸዋል የሚለው አንቀጽ ተሰርዞ በመቅረቡ ነው። የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ይህን የሕግ ረቂቅ ይዞ ከገኔቭ ወደ አሥመራ

እንደተመለሰ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በንጉሠ ነገሥቱ ልዩ አውሮፕላን ከአዲስ አበባ መጥተው፣ እጅግ አስቸጋሪ የሆነውን ድርድር ከመጀመራቸው በፊት፣ ስለ ኢትዮጵያ አቋም የሚከተለውን መግለጫ ሰጡ።

« ...... የኢትዮጵያንና የኤርትራን ሕዝቦች መሠረታዊ አንድነትና፣ አብሮ የመኖር አስፈላጊነት የተባበሩት መንግሥታት አምኖበት፣ የፌዴሬሽን አስተዳደር እንዲቋቋም ሲያደርግ፣ ሁለቱ አገሮች ኢትዮጵያና ኤርትራ በዩናይትድ ኔሽን ሞግዚትነት የሚተዳደሩ ናቸው ብሎ አይደለም። ኤርትራውያኖች እንደ ወንድሞቻቸው እንደ ኢትዮጵያውያኖች ሙሉ ነፃነት አላቸው። ወደፊትም ሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች፣ በጋራ ጉዳዮቻቸው ላይ ተነጋግረውና ተስማምተው፣ የሚያደርጉት ማናቸውም ውሳኔ ቢኖር፣ የተባበሩት መንግሥታትን አይመለከተውም። ..... ዩናይትድ ኔሽን፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል የሰጠውን ሪኮማንዳሲዮን (RECOMMANDATION) አክብረን መቀበላችንን በሚገባ አረጋግጠን ቃል ሰጥተናል። ነገር ግን ከዚህ ውጭ ወደፊት ስለሚኖረን አስተያየትና አሠራር፣ የዩናይትድ ኔሽን ጥገኛ እንድንሆን በሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ላይ የቀረበውን ሀሳብ፣ ኢትዮጵያ አትቀበለውም። ....... ባለፈው ዓመት በኒውዮርክ ስብሰባችን ላይ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ በሚጸድቅበት ጊዜ፣ አሁን በተባለው መልክ ከጣልያን ወገኖች የተሰነዘረውን የተንኮል ሀሳብ፣ ኢትዮጵያ እንደማትቀበለው በሚገባ አስረድታ ጉዳዩ ተዘግቶ ነበር። አሁን ደግሞ ይኸው ጣልያን የሚጭረው ሀሳብ፣ በሌላ በር ዞሮ ቀርቦ ስለአየነው፣ አለመቀበላችን ብቻ ሳይሆን፣ አጥብቀን የምናወግዘው መሆናችንንም እንዲታወቅ እንፈልጋለን። ከሕገ መንግሥቱ አዘጋጅ ከኮሚሽነር ማቲየንሶ ጋር በጠለቀ አስተያየት ተነጋግረንበት ችግሩን ብናስወግደው ደስ ይለኛል። ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ፣ ከፍ ካለ ቅሬታ ጋር በተባበሩት መንግሥታት ሸንጐ ላይ ቀርበን፣ በጀርባ እየተጐነጐነ የሚመጣብንን የጠላት ተንኮል ለመቋቋም ዝግጁ ነን። ....... ሁለተኛ፣ ፓርለማው የሚያወጣቸው ሕጐች በንጉሠ ነገሥቱ መጽደቅ አለባቸው። በተለይም አንዳንዶቹ ሕጐች የፌዴራሉን የኢትዮጵያን መንግሥት የሥልጣን ድርሻዎች የሚመለከቱ ሆነው ከተገኙና፣ ንጉሠ ነገሥቱ የማይስማሙበት ከሆነ፣ የቬቶ ሥልጣን እንደሚኖራቸው፣ ቀደም ሲል ከኮሚሽነሩ ጋር ተስማምተንበት ነበር። አሁን ይህን ሀሳብ፣ ዤኔቭ ሆነው ባሻሻሉት ረቂቅ ላይ ሰርዘውት በማየቴ በጣም አዝኛለሁ። በዚህ ጉዳይ የንጉሠ ነገሥቱን የቬቶ ሥልጣን መሰረዝ፣ ጠቅላላውን የፌዴሬሽኑን የአስተዳደር መንፈስ የሚያናጋው ስለሆነ አንቀበለውም። ....... »

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይህን ጠንካራ አቋም ይዘው፣ ከተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ጋር ለሁለት ስዓት በዝግ ስብሰባ ባደረጉት ድርድር፣ በመጨረሻ ከስምምነት ላይ ደርሰው፣ በመግባባትና በመከባበር መንፈስ ተለያዩ። ይህ ውጤት በመገኘቱ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን እጅግ አስደስቷቸው ነበር። የሁለቱ ሰዎች አለመግባባቷ በተፈጠረ ሰሞን፣ በአሥመራ ያሉት የፖለቲካ ታዛቢዎች በነበራቸው አስተያየት፣ የአክሊሉና የማቲየንሶ አቋም እጅግ የተራራቀ ስለሆነ፣ ኮሚሽነሩ ተናዶ የአሥመራ ቢሮውን እንደሚለቅና ወደ ኒውዮርክ ሄዶ ጉዳዩን ለተባበሩት መንግሥታት እንደሚያቀርብ ይጠብቁ ነበር። በተጨማሪም፣ የሁለቱ ሰዎች አለመግባባት የኤርትራን ጉዳይ እንደሚያበላሸው እና ኢትዮጵያም ብዙ ለፍታ ያገኘችውን ውጤት እንደሚያስናክልባት ተገምቶ ነበር።

ኮሚሽነር ማቲየንሶ ምንም እንኳ የጣልያን መንግሥትና የወገኖቹ የላቲኖች ድጋፍ እንደሚኖረው ቢተማመንም፣ በተባበሩት መንግሥታት ሸንጎ ላይ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መቋቋም እንደሚያዳግተው ያውቃል። እነ ኮምት ስፎርሳና እነ ኤንሪኮ ቸሩሊ፣ እነ ዮሴ አርሴና እነ አልቤርቶ ታርኪያኒ፣ በዓለም ማህበር አደባባይ ላይ ኢትዮጵያን ለማጥቃት ሲሞክሩ፣ ምን እንደደረሰባቸው አንሴ ማቲየንሶ በዓይኑ አይቷል። በጆሮውም ሰምቷል። ስለዚህ ምንም እንኳ የፌዴራሉን ሥልጣን ለማዳከምና የኢትዮጵያን መንግሥት ቅር ለማሰኘት ቢሞክርም፣ «ከጠበቃ» አከሊሉ ጋር ሙግት ለመግጠም ወደ ኒውዮርክ መመለስ አይፈልግም።

አንሴ ማቲየንሶ፣ በኤርትራ ሕዝብ ተወካዮች ተመርምሮ እንዲወሰንና ከዚያም በንጉሠ ነገሥቱ እንዲጸድቅ ባዘጋጀው ረቂቅ ሕገ መንግሥት ዝርዝር ውስጥ፣ የአንድነት ወገኖች ያመለከቷቸውን ሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች አላቀረባቸውም። እነዚህም፣ <u>አንደኛ/ ንጉሠ ነገሥቱ የኤርትራን የውስጥ መንግሥት መሪ እንዲሾሙና እንዲሽሩ፣ ሁለተኛ/ የኤርትራ የሥራ ቋንቋዎች ትግርኛና አማርኛ እንዲሆኑ፤ ሶስተኛ/ የኢትዮጵያዊት ኤርትራ ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሆነው የእናት አገር ባንዲራ እንዲሆን፣ የተባሉት ናቸው።</u> በእነዚህ ሶስት ጉዳዮች ላይ ኮሚሽነሩ የተከተለው ከተቃዋሚዎቹ ወገኖች የቀረቡለትን ሀሳብ መሆኑ፣ በረቂቁ ሕገ መንግሥት ላይ ሠፍሮ ታይቷል።

ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም፣ የተባበሩት መንግሥታት ባደረገው ውሳኔ፣ አገሪቱን የሚያስተዳድረው የቃላቁ ብሪታንያ መንግሥት፣ የመላ ኤርትራን ሕዝብ ተወካዮች አስመርጦ፣ ሕገ መንግሥቱን ለመወሰን እንዲሰበሰቡ እንዲያደርግ፣ አደራ የተጣለበት መሆኑ ይታወሳል። በዚሁ መሠረት፣ በመጋቢት እና ሚያዝያ ወራት 1952 ዓ.ም የመማክርቶቹ ምርጫ ሲከናወን ሰነበተ። ቀደም ሲል የአንድነት ወገኖች እንዳሳሰቡት፣ የኤርትራ ሕዝብ ወኪሎቹን በቀጥታ የመምረጥ፣ ችሎታውም ልምዱም ስለሌለው፣ ከአሥመራና ከምፅዋ ነዋሪዎች በስተቀር፣ በሌሎቹ ሥፍራዎች መማክርቶቹ የሚመረጡት፣ በታወቁ የሕዝብ ተጠሪዎችና ያገር ሽማግሌዎች አማካይነት እንዲሆን ተደረገ። እንደሚታወቀው እንግሊዞች ለአንድ አገር ምንም እንኳ አልፎ አልፎ ቅን ለማሰብ ቢያዘነብሉም፣ አንዳንድ የተንኮል ጥበባቸው የማይለያቸው ስለሆነ፣ የሕዝቡን መማክርቶች ሲያስመርጡ፣ በሀይማኖት ረገድ አገሩን በሁለት ከፍለው፣ ተመራጮቹ ሠላሣ አራት (34) ክርስቲያኖችና ሠላሣ አራት (34) እስላሞች እንዲሆኑ አደረጉ። ከእስላሞቹም መካከል፣ በዚያን ሰዓት ከማንም ወገን ድጋፍ አጥቶ ሜዳ ላይ የቀረውን ኢብራሂም ሡልጣንን፣ ለተንኮል መጠቀሚያ ይሆነናል ብለው በእነሱ ከፍተኛ ድጋፍ አስመረጡት። በዚህ አሠራር፣ የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነርም ከእንግሊዞቹ አስተዳዳሪዎች ጋር በሚገባ ተባብሯል። የእስላሞቹና የክርስቲያኖቹ ተመራጮች እኩል ለእኩል በመሆናቸው፣ (34 + 34) የአንድነቶችን ኃይል ለመቀነስና፣ የማቲየንሶ ሕገ መንግሥት ያለ ችግር ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚረዳ ሆኗል። የመማክርቶቹ ምርጫ የተከናወነው፣ በየአውራጃው ባለው የሕዝብ ብዛት መሠረት ተደልድሎ ቢሆን ኖሮ፣ የቆላው ዘላን ሕዝብ ተመራጮች፣ ቁጥራቸው እጅግ ያንስ ነበር። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ፣ በምክር ቤቱ አዳራሽ ከተዘጋጁት ስልሣ ስምንት (68) ወንበሮች ውስጥ፣ አብዛኛውን መቀመጫ የሚይዙት አንድነቶች ስለሚሆኑ፣ በሕገ መንግሥቱ ላይ በተለይ ስለ ለኤርትራ መሪ አመራረጥ ወይም አሿሿም፣ በቋንቋዎችና በባንዲራው ጉዳይ፣ በማቲየንሶ ተደግፎ የቀረበው የተቃዋሚዎቹ ሀሳብ፣ ሊለወጥም ሊሰረዝም ይችል ነበር።




ስለ ሕገ መንግሥቱ ዝግጅት ከማቲየንሶ ጋር ለመነጋገር አክሊሉ ሀብተወልድ አሥመራ ሲደርሱ ኮሚሽነሩ ሲቀበላቸው፤

*« ....... ስለ ፌዴሬሽኑ አሠራር የዩናይትድ ኔሽን ጥገኛ እንድንሆን፤ በሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ላይ የተገለጸውን ሀሳብ፤ ኢትዮጵያ አትቀበለውም ....... »*

(አክሊሉ ሀብተወልድ የካቲት 1950 አሥመራ)

## የቋንቋና የባንዲራው ጉዳይ

በኤርትራ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመረጡት የስልሣ ስምንቱ የሕዝብ ተወካዮች ስብሰባ፣ በእንግሊዙ አስተዳዳሪ በጀኔራል ደንከን ካሚንግ (GENERAL DUNCAN CUMMING) ሚያዝያ 29 ቀን 1952 ዓ.ም በአፈስየል ከተከፈተ በኋላ፣

1. አቶ ተድላ ባይሩ -- የአንድነት ማህበር ዋና ጸሐፊ፣ የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት፣

2. ሼህ ዓሊ ሙሣ ራዳይ -- የምዕራባዊው ቆላ የእስላም ሊግ መሪ፣ የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ እንዲሆኑ፣ የመጀመሪያዉ በ49፣ ሁለተኛው በ48 ድምፅ ብልጫ ተመረጡ።

በማቲየንሶ ከተዘጋጁት ዘጠና ዘጠኝ (99) የሕገ መንግሥት አንቀጾች ውስጥ፣ የመማክርቶቹን ስምምነት ለማግኘት እጅግ አጨቃጫቂና አስቸጋሪ ሆነው የተገኙት፣ ለኤርትራ ስለሚወስነው የኦፊሲየል ቋንቋና የፌዴሬሽኑን ባንዲራ የሚመለከቱት ጉዳዮች ነበሩ። ለኤርትራ ሕዝብ የሚያገለግሉት የሥራ ቋንቋዎች፣ <u>ትግርኛ፣ ዓረብኛና ጣልያንኛ</u> እንዲሆኑ ከልዩ ልዩ ሰዎች በቀረቡት ሀሳቦች ላይ፣ ከመማክርቶቹ ውስጥ የመጀመሪያው ተናጋሪ በመሆን፣ መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም የሚከተለውን አስተያየት ሰጡ።

« ....... ክቡር ኮሚሽነር ደህና አድርገው እንደሚያውቁት፣ ዓረብኛና ጣልያንኛ ለኛ ለኤርትራውያኖች የባዕድ ቋንቋዎች ናቸው። በተለይ ጣልያንኛ ከቁም ነገሩ ውስጥ ተጠቅሶ ማየቱ እጅግ አሳዝኖኛል። ...... ክቡር ኮሚሽነር እንደሚያውቁትና፣ በዓለም ታሪክ ላይ እንደሚታየው፣ የጥንቶቹ ቅኝ ገዥዎች የሰው አገርና ሕዝብ በኃይል ይዘው በጭቆና ከመግዛታቸውም በላይ፣ የአገሩ ሕዝብ ባሕሉንና ቋንቋውን አጥቶ፣ የገዥዎቹን ባሕልና ቋንቋ ለብሶት ለዘለዓለሙ እንዲኖር አድርገውታል። ...... ፈጣሪ ይመሥገን፣ በእኛ በኤርትራውያኖች ላይ የደረሰው የጣልያን የቅኝ አገዛዝ፣ መሠረታዊ ባሕላችንን እና ቋንቋችንን አጥፍቶ በጣልያንኛ ለመተካት አልቻለም። ስለዚህ፣ በምንም ምክንያት የጠላታችን የጣልያን ቋንቋ እና እንዲሁም ለኛ ለኤርትራውያኖች ባዕድ የሆነው ዓረብኛ፣ ሕገ መንግሥታችን ውስጥ መግባት የለባቸውም። ...... ክቡር ኮሚሽነር እንደሚያውቁት አሁንም ፈጣሪ ይመሥገን፣ የተባበሩት መንግሥታት ለኛ ለኤርትራውያን ባዘጋጁልን የአስተዳደር ሕግ፣ ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መሆናችንን አረጋግጠልናል። ሁላችንም የአንዲት ኢትዮጵያ ዜጐች መሆናችን በሕግ ተወስኖልናል። ስለዚህ፣ የኛ የኤርትራውያኖች የውስጥ አስተዳደራችን ቋንቋ ትግርኛ ሆኖ፣ የፌዴራል መንግሥታችን የኢትዮጵያ መሥሪያ ቋንቋ የሆነው አማርኛ ቢገባ፣ የተባበሩት መንግሥታት ከሰጠው ውሳኔ ጋር የሚስማማ ስለሆነ፣ ሀሳቤ እንዲመዘገብልኝ እጠይቃለሁ ....... »

መላከሠላም ዲሚጥሮስ፣ ይህን አስተያየታቸውን በሚገልጡበት ጊዜ ከተቃዋሚዎቹ ከእነ ኢብራሂም ሡልጣን ስፈር ጩኸትና ፉጨት ቢሰማም፣ የአንድነቶች ጭብጨባ የስብሰባውን አዳራሽ አግሎት ነበር። ኮሚሽነሩም ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ፣ « ...... የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት አሁን በሚሠራበት ሕገ መንግሥት ላይ፣ አማርኛ የኢትዮጵያ የኦፊሲየል ቋንቋ ነው



አክሊሉና ማቲየንሶ ከብዙ ክርክር በኋላ፣ በሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ላይ ተስማምተው፣ ደስታቸውን ሲገላለጡ።

(አሥመራ የካቲት 1950 ዓ.ም)

አልተባለም:: ...... የኤርትራ ሕዝብ በተሰጠው የአቶኖሚ መብት፣ ለውስጥ አስተዳደሩ ትግርኛን እና ዓረብኛን እንዲጠቀምበት የበኩላችንን ምክር እንሰጣለን ....... » የሚል አስተያየት አቀረበ::

መላከሠላም፣ የተሰጣቸውን መልስ አጥጋቢ ሆኖ አላገኙትም:: በመሠረቱ ለአንድ አገር ሕዝብ የሚያስፈልገውን የሥራ ቋንቋ፣ የተባበሩት መንግሥታት መራጭና መካሪ መሆን አይገባውም ነበር:: በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አማርኛ የነገሥታቱና [illegible] ሀገሩ አስተዳዳሪዎች መገናኛ ቋንቋ ሆኖ የኖረ ነው:: ለምሳሌም ያህል መላ ኢትዮጵያን፣ ለአስራ ሰባት ዓመታት የገዙት ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ አራተኛ፣ የመንግሥታቸውኦፊሲየል ቋንቋ አማርኛ ነበር:: በ1930 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያጸደቁት ሕገ መንግሥት፣ አማርኛ የሥራ ቋንቋ መሆኑ አልተጠቀሰም ተብሎ፣ ኮሚሽኑ የቀረበው ምክንያት በተንኮለኞች የተጠነሰሰ ነው በማለት መላከ ሰላም እና ወገኖቻቸው አዝነዋል:: በመጨረሻው በብላታ ደምሣስ ወልደሚካኤል ጠያቂነት፣ የጣልያንኛ ቋንቋ እንዲሰረዝ ቢደረግም፣ ከብዙ ክርክር በኋላ በድምፅ ብልጫ ዓረብኛን አስቀርቶ አማርኛን ለመተካት አልተቻለም:: ዓምደሚካኤል ደጝስኝ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በላኩት ቴሌግራም፣ ዓረብኛን አስቀርቶ ትግርኛን ብቻ የሥራ ቋንቋ ለማድረግ ትንሽ ዕድል እንደነበረ ጠቁመው፣ ነገር ግን የአጥባቂ አንድነት ወገኖች፣ በዓረብኛ ቦታ አማርኛን ለማስገባት ብዙ ስለታገሉ፣ የእስላሞቹ ኃይል መዝኖ በመጨረሻ ትግርኛና ዓረብኛ የኦፊሲየል ቋንቋዎች እንዲሆኑ በመጠነኛ ድምፅ ብልጫ መወሰኑን ገልጸዋል::

## ትልቁ ብጥብጥ በባንዲራው ጉዳይ ነበር

የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ከጣልያኖች የተሰጠውን ምክር ተቀብሎ እሳቱን ባይጭር ኖሮ፣ በመላ ኤርትራ የሚውለበለበው፣አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ከሆነው ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በስተቀር፣ ሌላ ባንዲራ አይታሰብም ነበር:: የተባበሩት መንግሥታት የሰጠው ውሳኔ፣ ኤርትራ በኢትዮጵያ ዘውድ ሥር አቶኖሚ ያለው አስተዳደር እንዲኖራት ነው እንጂ፣ በሁለት የባዕድ አገሮች መካከል እንደሚዋቀር ፌዴሬሽን ዓይነት ታስቦ አልነበረም:: የኤርትራ ሕዝብ፣ የቅኝ አስተዳዳሪዎቹን ግፍ በሚቀበልበት ዘመን፣ ለሀዘኑም ሆነ ለደስታው የኢትዮጵያዊነቱን ስሜት የሚገልጸው፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሆነውን ባንዲራ አንግቦ ነው:: ሰው ሲሞት የአስከሬኑ ሣጥን የሚጎናፈጸው፣ ሠርግና ልዩ ልዩ የሕብረሰብ በዓላት በሚፈጸምበት የዳስ አዳራሽ ላይ፣ ተንዠርግጎ ድምቀት እንዲሰጥ የሚደረገው፣ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ነበር:: የኮሎኒያሊስትና የፋሽስት ካራቢኒየሬ ወታደሮች፣ ይህን ባንዲራ ለምን ይዛችሁ ታያችሁ ? እያሉ፣ ሕዝቡን በሚያስቃዩበት ጊዜ፣ « ...... እነዚህ ሶስቱ ሕብረ ቀለማት፣ የሀይማኖታችን ምልክቶች ስለሆኑ እንለውጣቸውም ........ » በማለት፣ በድፍረት ሲታገሉ የተገደሉት ኤርትራውያኖች እጅግ ብዙዎች ናቸው::

የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር፣ ስለ ሰንደቅ ዓላማው ጉዳይ የሕዝቡ መሠረታዊ ስሜት ምን እንደሆነ በሰፊው ቢገለጽለትም፣ በጣም ጥቂቶች የሆኑትን ተቃዋሚዎችና በተለይም ጣልያኖቹን ለማስደሰት፣ ለኤርትራ የተለየ ባንዲራ እንዲኖራት፣ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ሀያ አንድ ላይ (21) አርቅቆ አቀረበ::



በማቲየንሶ የተዘጋጀው የኤርትራ ሕገ መንግሥት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኦፊሲየል በቀረበበት ዕለት፣

ከግራ ወደ ቀኝ አንሴ ማቲየንሶ፣ እንግሊዛዊው አስተዳደሪ ዤኔራል ካሚንግ፣ የጃንሆይ ላይዘን ኦፊሰር ዓምደሚካኤል ደሣለኝ፣

(አሥመራ መጋቢት 1952)

እንድነቶች፣ ኤርትራ ከእናቷ ከኢትዮጵያ፣ የተለየ ባንዲራ የላትም ብለው በንዴት ሲግሉ፣ እስላሞቹ ደግሞ በተንከለኞች እንደተመከሩት፣ የተባበሩት መንግሥታት ለኤርትራ ሕዝብ ለሰጠው መብት ዋና ምልክት የሆነው የፌዴሬሽኑ ባንዲራ ካልኖረ አሻፈረን አሉ:: ቀደም ሲል የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ወደ ኤርትራ በመጣ ጊዜ፣ በሁለቱ ወገኖች በአንድነቶቹና በእስላም ሊግ አባሎች መካከል፣ ሁለቱም በየአቋማቸው ተከባብረው በሠላም **ለመኖር** ያደረጉት ስምምነት ደፍርሶ ሁኔታው ወደ ጠብ አመራ:: እንድነቶች፣ **በቀኛ**ማናው ቄስ ዲሚጥሮስ ተቀዳሚነት፣ የስብሰባው**ን** አዳራሽ ለቀው ወጡ:: **መፈክሩም**:

« ..... ያንድነት ወገን የሆንክ ሁሉ እጅህን አንሳ ! **እስከ** ዛሬ ድረስ ደምህን እያፈሰስክ ጠብቀህ ለያዝከት የኢትዮጵያ ባንዲራ፣ **ዛሬም** መስዋዕት ለመሆን ተዘጋጅላት ..... » የሚል ነበር:: ጠቅላላው ሁኔታ **እጅግ** የሚያሳስብ ሆነ:: አሥመራ፣ ባሩድ ባሩድ ለመሽተት የተቃረበች ሆነች:: **ከአዲስ** አበባ ከአቶ አስፍሐ ወልደሚካኤል ጋር ሽማግሌዎች እየገሰገሱ አሥመራ **ደርሰው**፣ ጠቡን አብርደው ሠላም ለመፍጠር ጥረታቸውን ቀጠሉ::

አቶ ዓምደሚካኤል ደሣለኝ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ላይዘን ኦፊሰር፣ እንድነቶች ወደ ተሰበሰቡበት አደባባይ ቀርበው በሰጡት **ማብራሪያ**፣ « ..... በረቂቁ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 21 ላይ እንደተጠቀሰው፣ ሶስቱ ቀለማት የሆነው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በመላ ኤርትራ የተከበረ ሆኖ ይውለበለባል:: ይህ ለኤርትራ የተባለው ባንዲራ ለፌዴሬሽኑ አስተዳደር ምልክት እንዲሆን ከኢትዮጵያ ባንዲራ አጠገብ የሚሰቀል ነው እንጂ፣ ሌላ ትርጉም እንደሌለው አረጋግጣለሁ:: እኛም ይህንን የተቀበልነው፣ በለውጡ ለኤርትራ የውስጥ መንግሥት መሪ ሆኖ የሚመረጠው፣ ከእንድነቶች ወገን እንዲሆን፣ ከራቢጣዎቹ ጋር የውስጥ ስምምነት በማድረግ ስለሆነ፣ የፌዴሬሽኑ ምልክት ለተባለው ባንዲራ ጉዳይ ቁም ነገር መስጠት አይገባም ...... » አሉ:: ወጣቱ ዓምደሚካኤል ደሣለኝ፣ የገነፈለውን ቁጣ ለማብረድ ብለው የሰጡት ማብራሪያ፣ እንድነቶችን የበለጠ ወደ ብስጭት መራቸው:: ወዲያው፣ የእምቢተኞቹ አፈ ጉባኤ የሆኑት መላከሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም፣ እንባ እየተናነቃቸው፣ « ..... እኛ ኤርትራውያን ዕድሜያችንን ሙሉ ስቃይ ስንቀበልና ስንሰዋ የኖርነው ለማን ነው ? ..... ለኢትዮጵያዊነት ምልክታችን፣ ለአረንጓዴ፣ ቢጫ ቀይ ባንዲራችን አልነበረም ወይ? ...... ሕይወታችን አድርገን የምናመልክባትን ባንዲራችንን ይዘን፣ ለምን የመንግሥት መሪነቱን ሥልጣን እነ ኢብራሂም ሡልጣን አይረከቡትም ? ..... ለእኛ ከሁሉም የምትበልጥብን ኢትዮጵያዊቷ ባንዲራችን ስለሆነች፣ ለጊዜያዊ ሥልጣን አንለውጣትም:: ..... ለካስ ውስጥ ውስጡን ከጠላቶቻችን ጋር እየመከራችሁ፣ እዚህ ውርደት ላይ የምትጥሉን እናንተ ኖርዋችኋል ? ...... » ብለው ዓይናቸውን ዓምደሚካኤል ላይ ሲተክሉ፣ እንድነቶች እጅግ በጋለ ድምፅ ፣ « ...... ኮሎኔል ነጋን መልሱልን:: ዓምደሚካኤልን ውሰዱልን ....... » የሚል ጩኸት ማቀጣጠል ጀመሩ:: በዚህ መልክ የተቀሰቀሰውን ንዴት፣ የንጉሡ ነገሥቱ ላይዘን ኦፊሰር ለመመከት የማይችሉ መሆናቸውን ሲረዱት፣ ለጊዜው ዘወር ማለት አስፈላጊያቸው ሆነ:: ወዲያው፣ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ « ንጉሡ ነገሥቱ ለአንድነቶች የላኩትን ልዩ መልዕክት እንዳነብላችሁ ፍቀዱልኝ » ብለው ቀረቡ:: ቃሉም የሚከተለው ነበር::

« ..... ከዚህ ቀደም ደጋግመን እንደገለጽንላችሁ፣ የሕይወታችንን መቆየት የምንመኘው፣ ተለያይተው የሚኖሩትን እናትና ልጆች ኢትዮጵያንና ኤርትራን አንድ ለማድረግ ነው:: ለስልሣ ዓመታት የኤርትራ ሕዝባችን ከእናት አገሩ

ተለይቶ በኮሎኒያሊስት ጣልያን የግፍ አገዛዝ ያሳለፈው ሥቃይ፣ ራሱን የቻለ አንድ ትልቅ ታሪክ ስለሆነ፣ በዚህ ጥቂቱ በምንልክላችሁ መልዕክት ሊዘረዘር አይችልም። ከአራቱ ኃያላን አገሮችና ሰላም ከሚሆኑት ከተባበሩት መንግሥታት ጋር ታግለን ያገኘነው ውጤት፣ በእናንተ በታማኝ ዜጎቻችን ቆራጥነትና መስዋዕትነት እየተረዳን መሆኑን ልንጠቅሰው እንወዳለን። እንደምታውቁት ፌዴራሲዮን የተባለው ነገር፣ የኛና የመንግሥታችን፣ የናንተም የታማኝ ዜጎቻችን ጥያቄም ፍላጐትም አይደለም። ጊዜ በማጥፋት ለጠላቶቻችን ዕድል እንዳንሰጥ በማለት፣ ይህን ያልተሟላ ፍርድ ከተባበሩት መንግሥታት የተቀበልነው፣ ወደፊት ሁኔታው በሚፈጥረውና በሚኖረን መንገድ፣ ከፈጣሪያችን እርዳታ እና ከእናንተም ከታማኞቻችን ቆራጥነት ጋር፣ ከምናስበው ለመድረስ እንደምንችል ጽኑ ዕምነት ስለአለን ነው። ስለዚህ፤ አንደኛ/ አሁን ኤርትራን በሥልጣን የሚያስተዳድረው መንግሥት፤ (እንግሊዝ) አስፈላጊውን ሁሉ በሠላምና በወዳጅነት አስረክቦን ኤርትራን እስከሚለቅበት ድረስ፤ ሁለተኛ/ ከተባበሩት መንግሥታት ጋር ባለን ግንኙነት፣ የተሰጠውን ውሳኔ በተግባር ለማዋል የሚያስችለንን ድርድር ጨርሰን፣ በሠላም እስከምንለያይበት ጊዜ ድረስ፣ ለማናቸውም ጉዳይ ትዕግሥታችሁ የጠነከረ፣ አቋማችሁ ለፍርድ የሚመች ጨዋ የሆነ መንገድ የተከተለ፣ እንዲሆን አደራ እንላችኋለን። የናንተ ሀሳብና ምኞት ምን እንደሆነ፣ በሚገባ እንደተረዳነው ሁሉ፣ እናንተም እኛ በምንሰጣችሁ መምሪያ ዕምነታችሁ የጸና መሆኑን በሚገባ እናውቃለን። የምናስበው ሁሉ ጊዜውን ጠብቆ እንደሚፈጸም፣ ሁሉን የሚችል እምላክ አይለየንም ብለን ተስፋ እናደርጋለን ....... »

አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በተለይ ከንጉሠ ነገሥቱ የታዘዝኩት ንጉሣዊ መልዕክት ነው ብለው፣ በብዕራቸው ጽፈው ያነበቡት ቃል፣ ጠቡን ወደ ሠላም ለመለወጥ ፍቱን መድኃኒት ሆነ። ወዲያውም፤ አንድነቶች ቁጣቸውን አብርደው፣ የንጉሠ ነገሥታችንን ትዕዛዝ ማክበር አለብን ብለው ከወሰኑ በኋላ፣ ወደ ስብሰባው አዳራሽ በሠላም ተመልሰው መንበሮቻቸውን ያዙ። ጉባኤውም፤ ያችን ስለ ባንዲራ ጉዳይ በማቲየንሶ የተዘጋጀችውን አንቀጽ ሀያ አንድ፣ (21) በአንድነቶች ዝምታ፣ በራቢጣዎች የድጋፍ ሆሆታ አጽድቆ፣ ወደ ሌሎቹ ጉዳዮች በሠላም ተሻገረ።

በዘጠና ዘጠኝ (99) አንቀጾች በተተነተነው ሕገ መንግሥት ውስጥ፣ የማቲየንሶ ሥልጣን፣ የኢትዮጵያን መንግሥት ቅር አስኝቶ ጣልያኖቹንና ራቢጣዎቹን ማርካት የቻለው፣ የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው የፌዴራል አክት ሬዞሉሽን ላይ፣ ተብራርተው ባልተጠቀሱት ስስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ነው። እነዚህም ቀደም ሲል ተደጋግመው እንደተገለጹት፤

አንደኛ/ ስለ ኤርትራ የውስጥ መንግሥት መሪ አሿሿም፣
ሁለተኛ/ ለመንግሥቱ አመራር የሥራ ቋንቋዎች አመራረጥ፣
ሶስተኛ/ ስለ ፌዴሬሽን ባንዲራ መኖር አለመኖር፤ ናቸው።

በሥራ ቋንቋዎች አመራረጥ ላይ ከትግርኛ ቀጥሎ ዓረብኛ እንዲገባ፤ በመማክርቶቹ ጉባኤ ላይ የማቲየንሶ ምክር ስጭነት፤ ትክክል አለመሆኑን የታዘቡት ብዙዎች ናቸው። የኤርትራ እስላሞች ትግሬ እና ትግርኛ የሚናገሩ ናቸው እንጂ፣ ለሀይማኖታቸው ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ዓረብኛ ቋንቋቸው አይደለም። በኤርትራ አስተዳደር ከፍተኛ ለሆኑት ጉዳዮች ባለሥልጣን የሆነውን የፌዴራሉን የኢትዮጵያን መንግሥት የሥራ ቋንቋ፤ የአቶኖሚው አስተዳደር እንዲቀበል አለመደረጉ፣ እጅግ አስገራሚ ሆኖ ተገምቷል። የሆነ ሆኖ የማቲየንሶ ሕገ

መንግሥት የኤርትራ የሥራ ቋንቋዎች ትግርኛ እና ዓረብኛ ብቻ እንዲሆኑ ቢወስንም፣ በአሥሩ ዓመታት የፌዴሬሽን አስተዳደር ዘመን እንደታየው፣ ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር ላሉት ግንኙነቶች በሙሉ፣ አማርኛ የኦፊሲየል ቋንቋ ሆኖ ተሰርቶበታል:: ቀጥሎም የፌዴሬሽን ባንዲራ እንዲኖር ሀሳቡ የመነጨው ከኤርትራውያኖች ሳይሆን፣ ከጣልያን አማካሪዎቹ የተጫረለትን እሳት አራግቦ ለፍም ያደረሰው ማቲየንሶ ነው:: ቀደም ሲል እንደታየው ከሁሉ ይበልጥ የአንድነቶችን አንጀት አጅግ ያሳረረው፣ የባንዲራ መለዮ በመደረጉ ነበር::

ዓምደሚካኤል ደሣለኝ፣ ለንጉሠ ነገሥቱና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በላኩት ራፖር፣ በሕገ መንግሥቱ ላይ ከተመዘገቡት ዘጠና ዘጠኝ አንቀጾች ውስጥ፣ ለፌዴራሉ መንግሥት ለኢትዮጵያ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው የሚሏቸው ሁለት ጉዳዮች ነበሩ:: እነዚህም፤ አንደኛው ለኤርትራ በጃንሆይ የሚሾመው የዘውድ እንደራሴ፣ ፓርለማው የሚደነግጋቸው ሕጐች ሁሉ ከመታወጃቸው በፊት፣ በንጉሠ ነገሥቱ ስም ሆኖ ለመፍቀድም፣ ለማገድም፣ ሥልጣን እንዲኖረው መደረጉ ሲሆን፣ ሁለተኛው፤ ደግሞ በመማክርቶቹ መካከል በተደረገው የውስጥ ስምምነት መሠረት፣ የኤርትራ መሪ የሚመረጠው ከአንድነቶች ወገን ብቻ እንዲሆን በመታሰቡ ነበር::

ሕገ መንግሥቱ በንጉሠ ነገሥቱ ጸድቆ የፌዴሬሽኑን አስተዳደር የሚሸከመው ባቡር፣ ሀዲዱ ላይ መሽከርከር ሲጀምር፣ እነዚህ እንግሊዞች ያስመረጧቸው መማክርቶች ወደየቤታቸው እንዲመለሱ፣ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች ጽኑ ፍላጐት ነበር:: የእነሱ አስተያየት፣ እንግሊዞች ሥልጣናቸውን አስረክበው ኤርትራን እንደለቀቁ ወዲያውኑ ምርጫ ቢደረግ፣ የፓርላማው ወንበሮች የእስላምና የክርስቲያን እየተባለ መከፋፈሉ ቀርቶ ስማንያ በመቶው የአንድነቶች፣ ሀያ በመቶው የተቂቶች ራቢጣዎች ይሆናል የሚል ነው:: በላይዘን አፈስሩ ግምት ደግሞ፣ በመላ ኤርትራ ያሉት የእስልምና ተከታዮች፣ የአንድነት ደጋፊዎች ሆኑ ተቃዋሚዎች፣ ከክርስቲያኖች ወንድሞቻቸው ጋር በፓርለማው እኩል ወንበር እንዲያገኙ ካልተደረገ፣ የሚፈጠረው ችግር አጅግ ከባድ ይሆናል ተብሎ ታስቧል:: በኤርትራ ያሉት እስላሞች ቁጥራችን ከክርስቲያኖቹ ያነሰ ነው ብለው ጨርሶ አያምኑም:: የየሀይማኖቱ ተከታዮች ቁጥራቸው ምን ያህል መሆኑ በትክክል ባይታወቅም፣ በብዙ ሰዎች አስተያየት የሚነገረው፣ እስላሞቹና ክርስቲያኖቹ እኩል ለእኩል ናቸው ተብሎ ነው:: በዚህ አኳኋን የዓምደሚካኤል ደሣለኝ አስተያየት መሠረት እንደነበረው መገመት የሚያስችለው፤ ከአራት ዓመታት በኋላ፣ በመስከረም 1956 ዓ.ም የኤርትራ መንግሥት መሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ የሁለተኛውን የፓርለማ ምርጫ ሲያስፈጽሙ፣ ስልሣ ስምንቱን የምክር ቤት ወንበሮች ለክርስቲያኖቹና ለእስላሞቹ እኩል ለእኩል (34+34) እንዲከፋፈል ማስደረጋቸው ነው::

## ሕገ መንግሥቱ ሲጸድቅ፤ ማቲየንሶ ጣልያኖችን አመሰገነ

ነሐሴ 11 ቀን 1952 ዓ.ም አዲስ አበባ በታላቁ ቤተ መንግሥት አዳራሽ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለኤርትራ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ተዘጋጅቶ የሕዝቡ ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ የተቀበለውን ሕገ መንግሥት በንጉሠ ነገሥታዊ ፊርማቸው አጸደቁት:: በዚህ ከፍተኛ ሥነ ሥርዓት



*« ...... የታገልነውና የተሰዋነው ለባንዲራችን ነው። የኢትዮጵያ ባንዲራችንን ይዘን፣ ለምን ጠቅላይ ሚኒስትር እነ ኢብራሂም ሡልጣን አይሆኑም ...... »*

መላከሠላም ዲሚጥሮስ ገ/ማርያም
(አሥመራ ሐምሌ 1952)

ላይ፣ የሕገ መንግሥቱ ደራሲ የሆነው ኮሚሽነርና፣ የኤርትራ የታላቋ ብሪታንያ ወታደራዊ አስተዳደር መሪ የሆነው ጄኔራል ካሚንግ ተገኝተዋል።


ኤድዋርዶ አንሴ ማቲየንሶ (EDOARDO ANZE MATIENZO) ንግግሩን የከፈተው፤ « ..... ለኢትዮጵያ ዘውድ ሥልጣንና ለኤርትራ ሕዝብ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት፣ መሠረት የሆኑትን ሁለቱን የማዕዘን ድንጋዮች በተባበሩት መንግሥታት ስም ሆኜ ስተክላቸው፣ የግርማዊነትዎ መንግሥት እንደሚያከብራቸውና የፌዴራሉንም ድንጋጌዎች እንደሚሠራባቸው በሚገባ ተገንዝቤ ነው ...... » በሚል ቃል ነበር። ይህ አነጋገር የሚያመለክተው፣ ማቲየንሶ ከአሥራ ስምንት ወራት በኋላ አሁንም፤ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የፌዴራሲዮኑን አስተዳደር ሊያፈርሰው ይችላል የሚለው በአእምሮው ውስጥ የሚጉላላው ጥርጣሬ አለመወገዱን ነው። የሕገ መንግሥቱን ረቂቅ ሲያዘጋጅ፤ የፌዴራሉን አክት ሆነ የፌዴሬሽኑን አስተዳደር፣ ወደፊት ለመለወጥም ሆነ ለመሰረዝ፣ ሥልጣኑ የተባበሩት መንግሥታት ይሆናል የሚል አንቀጽ ባቀረበ ጊዜ፣ ኢትዮጵያ እንደማትቀበለውና ማቲየንሶም ይህን ሀሳብ ያመነጨው ከተሰጠው መምሪያ ውጭ ነው ተብሎ የጠነከረ አቋም ስለተወሰደበት፣ ዕቅዱን እንደሰረዘ ይታወሳል።

በዚህ በታላቁ ሥነ ሥርዓት ላይ ማቲየንሶ ባደረገው ንግግር፤ « ..... በግርማዊነትዎ ዘውድ ሥር፣ ኤርትራ በፌዴሬሲዮን ከኢትዮጵያ ጋር ተቀላቅላ፣ ዛሬ የውስጥ አስተዳደር ነፃነቷን ያገኘችበትን፣ ይህንን የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ፣ መላው የኤርትራ ሕዝብ በእውነተኛነትና በታማኝነት መቀበሉን በጥልቅ ተረድቼዋለሁ ...... » አለ። በንግግሩም ማክተሚያ ላይ፣ ኤርትራን ሲያስተዳድሩ ለቆዩት ለታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ባለሥልጣኖች መልካም አስተያየቱን ከገለጸ በኋላ፣ ማቲየንሶ ያለ እንዳች ይሉኝታ ለዲስኩሩ መደምደሚያ ያደረገው፣ <u>የተባበሩት መንግሥታት የሰጠውን ውሳኔ በመከተል፣ ከፍተኛ ትብብርና እርዳታ ለሰጡት ለጣልያን መንግሥትና፣ በኤርትራ ለሚኖሩት የጣልያን ዜጎች፣ ጥልቅ የሆነ ምሥጋናውን በማቅረብ ነበር</u>።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በማቲየንሶ ስሜት አገላለጽ ቢገረሙም፣ ማንኛውም ጉዳይ በሠላም አልቆ እንዲሸኝ፣ አስፈላጊነቱን አምነውበት ስለነበረ፣ ሕገ መንግሥቱን በማዘጋጀት የቦሊቪያው ተወላጅ የፈጸመውን ተግባር፣ በዲፕሎማሲ ቃላት ከማመስገን አልተቆጠቡም። ንጉሠ ነገሥቱ በንግግራቸው ውስጥ፣ የኤርትራን ምክር ቤት በፕሬዚዳንትነት ለመሩት ለአቶ ተድላ ባይሩ እና ለምክትል ሊቀመንበሩ ለሼህ ዓሊ ሙሣ ራዳይ፣ ችሎታቸውንና ትጋታቸውን በማድነቅ ካመሰገኗቸው በኋላ፤ « ..... ይህን የመተዳደሪያ ሕግ ለሰጠናቸው ለኤርትራውያን ዜጎቻችን የወደፊት ዕድል፣ ሁሉን የሚችል አምላክ በረከቱን እንዲሰጥ እንለምነዋለን ....... » ብለው፡ ሕገ መንግሥቱን በንጉሠ ነገሥታዊ ፊርማቸው አጸደቁ።

## በኤርትራ የንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ እንደራሴ

የማቲየንሶ ሕገ መንግሥት በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ ለኤርትራ የሚሾመው የንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ እንደራሴ ስለሚኖረው ሥልጣን ብዙ ክርክር ተፈጥሮ እንደነበረ ይታወሳል።



ቀ.ኃ.ሥ በጣልያንና በኢትዮጵያ መካከል የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ለመዘርጋት የመጣውን የውጭ ጉዳይ መክትል ሚኒስትር ጁሴፔ ብሩዛስካን ተቀብለው ሲያነጋግሩ።

*« ...... በድል አድርጊነት ስንመለስ፣ በአገራችን የነበሩትን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጣልያኖች፣ በክርስቲያን መንፈስ በመመራት አደጋም ሆነ ጉዳት እንዳያደርስባቸው፣ የሰጠነውን ትእዛዝ ሕዝባችን በሚገባ ፈጽሟል። ....... »*

(ቀ.ኃ.ሥ መስከረም 7 ቀን 1951 ዓ.ም)

የአንድነቶች ፍላጐት፣ የኤርትራን የውስጥ መንግሥት መሪ ንጉሠ ነገሥቱ እንዲሾሙና ባስፈለገም ጊዜ የመሻር ሥልጣን እንዲኖራቸው ስለሆነ፣ በመጀመሪያው ስሞን የዘውዱ እንደራሴ ስለሚኖረው ሥልጣን አልተጨነቁም ነበር። በመጨረሻው ያስቡት የሚሳካ አለመሆኑን ሲያውቁት፣ የዘውዱ እንደራሴ ሥልጣን እንዲጐላ ያስፈልጋል ብለው ተነሱ። የማቲየንሶ ሀሳብ ደግሞ፣ የንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ እንደራሴ፣ የፕሮቶኮል ሥነ ሥርዓት አድማቂ ከመሆን በስተቀር ሌላ ሚና ሊኖረው አይችልም የሚል ሆነ። ከብዙ ክርክር በኋላ፣ በሕገ መንግሥቱ ከ 10 እስከ 15 ድረስ ባሉት አንቀጾች ላይ እንደተጠቀሰው፣ የዘውዱ እንደራሴ የተወሰኑ ሥልጣኖች እንዲኖሩት ተደረገ።

ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ፣

1. የሕዝቡ ምክር ቤት የሚደነግጋቸው ሕጎች፣ የፌዴራሉን ሥልጣን የማይነኩ መሆናቸውን መርምሮ ካጣራ በኋላ እንዲታወጅ ያደርጋል። የተዘጋጀው የሕግ ረቂቅ ከፌዴራሉ መንግሥት ሥልጣን ጋር የሚጋጭ ከሆነ ደግሞ፣ እንዳይታወጅ ለማገድ ይችላል።

2. አዲስ ለሚሾመው የመንግሥት መሪ፣ (ቺፍ ኤግዜኩቲፍ) በፓርለማ የተደረገው አመራረጥ በተገቢው ሥነ ሥርዓት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ፣ ሹመቱን በንጉሠ ነገሥቱ ስም ተቀብሎ መሀላውን ያስፈጽማል። በጠ ላላውም የኤርትራ የውስጥ መንግሥት፣ በአስተዳደርና በልማት በኩል የሚያጋጥመውን ችግር እየመዘነ፣ ከአስተያየት ጋር ለፌዴራሉ መንግሥት ያቀርባል።

3. በዓመት ሁለት ጊዜ የፓርለማውን የሥራ ወቅት በንጉሠ ነገሥቱ ስም፣ የዘውድ ዲስኩር አድርጎ በኦፊሲየል ይከፍታል።

በዚህ አኳኋን ሕገ መንግሥቱ ጸድቆ በሥራ ላይ ለመዋል ሲቃረብ፣ ንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴያቸውን እስኪመርጡና ተሿሚው ማን መሆኑ እስኪታወቅ ድረስ፣ በአዲስ አበባ እና በኤርትራ ከፍ ባለ ጉጉት ይጠበቅ ነበር። የኤርትራን ሕዝብ ስሜትና መንፈስ በመመርኮዝ፣ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ልዑል አልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን እንዲሆኑ፣ አቶ ዘውዴ ገብረሕይወት የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር ለጃንሆይ አቀረቡ። በዚህ ሀሣብ፣ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስና አቶ መኰንን ሀብተወልድ ተስማምተዋል። ነገር ግን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ልጃቸውን ልዕልት ተናኘወርቅን በማሰብ በዚያን ጊዜ የጐንደር ጠቅላይ ገዥ የነበሩትን ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይን ለኤርትራ እንደራሴነት ማዘጋጀታቸው ስለተሰማ፣ እነዚህ ሁለቱ ታላላቅ ባለሥልጣኖች ዘውዴ ገብረሕይወት እንዳደረጉት፣ በቀጥታ ከጃንሆይ ጋር ተነጋግረው አልጋወራሽን ለማሾም አልሞከሩም። ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ፣ የጃንሆይ አማች በሆኑት በቢትወደድ አንዳርጌ ጉዳይ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ አስተያየት መስጠት አልፈለጉም። መኰንን ሀብተወልድ ደግሞ፣ በሁለቱ የጃንሆይ ልጆች መካከል -በተናኘወርቅና በአስፋወሰን? ለሚደረግ ምርጫ፣ ሳልጠየቅ ሀሳብ አቅራቢ አልሆንም አሉ። ዘውዴ ገብረሕይወት ግን የሥራ ረዳታቸውን ዓምደሚካኤል ደሣለኝን ይዘው ጣዕም ባለው አቀራረብ፣ የአልጋወራሽ የዘውድ እንደራሴነት ለፖለቲካውም ሆነ ለኤርትራ ሕዝብ ስሜት፣ በጣም ጠቃሚ መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ እንዲያምኑበት ለማድረግ በስፊው ታገሉ። ስለ አልጋወራሽ እጩነት ተባራሪ ወሬ እየተናፈስ አሥመራ ሲደርስ፣



አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ከፊታውራሪ ሐድጉ ፒላጋብር (ኋላ ደጃዝማች) ጋር፣

*« ....... ለኤርትራ ጉዳይ፣ የፌዴሬሽን መፍትሔ ከመቀበል በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ሌላ ምርጫ አልነበራትም ....... »*

አክሊሉ ሀብተወልድ
(አሥመራ የካቲት 1952 ዓ.ም)

እንኳንስ የአንድነት ወገኖች ቀርተው፥ ተቃዋሚዎች ነን የሚሉት የነ ራስ ተሰማ አስበሮም ቤተሰቦች ጭምር የድጋፍ አስተያየት መስጠት ጀመሩ። መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን፥ የኤርትራ ሕዝብ በቀጥታ አያውቃቸውም። ሆኖም፣ ንጉሠ ነገሥቱ እልጋ ወራሻቸውን እንደራሴያቸው አድርገው ቢሾሟቸው፥ በኤርትራ ባሉት የፖለቲካ መሪዎችና በሕዝቡ ዘንድ የሚሰጣቸው አክብሮት እጅግ ከፍ ያለ እንደሚሆን ታውቆ ነበር።

ዘውዴ ገብረሕይወት፥ ዓምደሚካኤል ደሣለኝንና አስፍሐ ወልደሚካኤልን ይዘው፥ ለአልጋወራሽ ሹመት የሚያደርጉት ጥረት፣ መሠረት ባለው ቁም ነገር ላይ ተመርኩዘው መሆኑን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሚገባ ተረድተውታል። ነገር ግን ለዚህ ታላቅ ቦታ አንድ ጊዜ አንዳርጋቸው መሣይን መርጠው ስለወሰኑ፣ ሀሳባቸውን መለወጥ አልፈለጉም። እጅግ ቅርቦቻቸው የሆኑት የወልደጊዮርጊስና የመኰንን ሀብተወልድ ዝምታ፣ ምክንያቱ ለምን እንደሆነ ያውቃሉ። ስለዚህ፣ እራሳቸው ያሰቡትን ለመፈጸም በሚያስችላቸው ረቂቅ በሆነው በተለመደ ጥበባቸው፥ ዘውዴ ገብረሕይወትን፣ እንዲሁም ዓምደሚካኤልንና አስፍሐን <u>በአንድነት በመሰብሰብ ሳይሆን፥ ለየብቻ እየጠሩ ማነጋገር ጀመሩ።</u> ለእያንዳንዳቸው የሚያቀርቡትም ጥያቄ፥ « ...... ለኤርትራ እንደራሴያችን አድርገን ለመሾም፣ በልጆቻችን በተናኘወርቅና በአስፋወሰን መካከል ልዩነቱ ምንድን ነው ሐ .... » የሚል ነበር። ዘውዴ ገብረሕይወት ከጠዋቱ በቆመበት ሀሳብ ጸኑ። አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በሁለቱ የጃንሆይ ልጆች መካከል የኤርትራ ሕዝብ ልዩነት አያደርግም አሉ። ከሁሉ ይበልጥ ወሳኙ፥ የዓምደሚካኤል አስተያየት ነበር። ክቡር ቢትወደድ የእንደራሴነቱን ተግባር በትክክል እንደሚፈጽሙ የታወቀ ነው። ልዕልት ተናኘወርቅ ደግሞ፥ በሕዝቡ ዘንድ ከሚኖራቸው የተለየ አክብሮት ሌላ፥ አኩልነት ተነፍጓቸው በጭቆና ለሚኖሩት የኤርትራ ሴቶች፥ እንደ እህቶቻቸው እንደ ኢትዮጵያውያኖች መብታቸውን ለማስከበር የልዕልትን እርዳታ ማግኘት ይችላሉ በማለት፥ ዓምደሚካኤል የተናገሩት ልብ የሚነካ ቃል፣ ንጉሠ ነገሥቱን ማበረታታት ብቻ ሳይሆን የበለጠም አስደሰተ። የዘውዴ ገብረሕይወት ሀሳብ ብቻውን ሆነ። ዓምደሚካኤልና አስፍሐ የጃንሆይን ስሜት በመከተል ከውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትሩ ስለተለዩ፥ የአልጋወራሽ የዘውድ እንደራሴነት ቀርቶ፥ የቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ ሹመት ተወስኖ በአዋጅ ተገለጠ።



ለኤርትራ የፌዴሬሽን መፍትሔ በተባበሩት መንግሥታት ከተወሰነ በኋላ፣ የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር አቶ ዘውዴ ገብረሕይወት የምዕራቡን ቆላ ሕዝብ ለማረጋጋትና ለማስተባበር አቀርዳትን በሚጐበኙበት ጊዜ፣ ከተቃዋሚው ወገን ከኢብራሂም ሡልጣን ጋር የተለዋወጧቸው ቃላቶች የሚጠቀሱ ሆነው አግኝተናቸዋል።

ዘውዴ ገ/ሕይወት፣ *« ...... ፈረስን ወደ ጅረት ያደርሱታል እንጂ፣ ውሃ አያጠጡትም ...... »*

ኢብራሂም፣ *« ...... በእኛ በኩል ፈረስን ጅረት ማድረስ ብቻ አይደለም። ውሃውን እንዲጠጣ እናግባብለዋለን ...... እናጭምለታለን ...... »*